# የዕብራውያን መጽሐፍ

## ትምህርት ሁለት

# ውቅርና ይዘት

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **የሚደጋገም ይዘት**

ሀ. የመጨረሻው ዘመን በኢየሱስ

ለ. የብሉይ ኪዳን ድጋፍ

1. ጭብጥ ዳራዎች
2. ነገረመለኮታዊ አመለካከቶች
3. የሞራል ግዴታዎች
4. ነገረ-ፍፃሜያዊ ትንቢቶች
5. ሥርወመንግሥታዊ ጭብጦች

ሐ. ስለመጽናት የተሰጠ ምክር

1. ምላሾች
2. ተነሳስቶዎች

3. **አሳማኝ አወቃቀር**

ሀ. የመላእክት መገለጥ

ለ. የሙሴ ሥልጣን

ሐ. የመልከጼዴቅ ክህነት

መ. አዲስ ኪዳን

ሠ. ተግባራዊ ጽናት

4. **ማጠቃለያ**

## መግቢያ

በተለያዩ ጉዳዮች ሰዎች ከሃሳባችን ጋር እንዲስማሙ ለማሳመን ስንጥር ራሳችንን የምናገኝበት ጊዜ ብዙ ነው፡፡ ይህንን የምናከናውንባቸው ብዙ መንገዶች አሉ፣ ከሁሉ ውጤታማ የሆነው ግን በተቻለ መጠን በጋራ በምንስማማበት የእምነት አቋም ላይ እየገነቡ መሄድ ነው፡፡ ከዚያም በጋራ መሠረታችን ላይ በመቆም፣ ስሌሎቹ ጉዳዮች ልናሳምናቸው እንጥራለን፡፡ በብዙ ገፅታውም፣ የዕብራውያን ጸሐፊም ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡ በአካባቢያቸው ወደተለመደው የአይሁድ ማኅበረሰብ አስተምህሮ በመመለስ ከመከራ ስጋት መትረፍን ምርጫዋ ለማድረግ እየተፈተነች ላለች ቤተክርስቲያን ነው የጻፈው፡፡ ስለዚህ፣ ለክርስቶስ በመታመን እንዲጸኑ ያሳስባቸዋል፣ ይህንንም የሚያደርገው በተቻለው መጠን እርሱና ተደራሲያኑ የጋራቸው በሆኑ የእምነት አቋሞች ላይ በመመሥረት ነው፡፡

ከዕብራውያን መጽሐፍ ተከታታይ ትምህርታችን ይህ ሁለተኛው ሲሆን "ይዘትና ውቅር" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ተደራሲያኑን ለክርስቶስ ወዳላቸው ታማኝነት እንዲመለሱ ለማሳመን እንዴት ይህንን አሳማኝ ስልት እንደተጠቀመ እንመለከታለን፡፡ በአወቃቀርና በይዘት ላይ ያተኮረው ይህ የዕብራውያን ትምህርት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ በመጽሐፉ ዐቢይ አንጓዎች ውስጥ ደጋግሞ የሚመጣውን ይዘት እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የዕብራውያንን አሳማኝ አወቃቀር በመመርመር፣ ጸሐፊው እነዚህን ተደጋጋሚ ይዘቶች እንዴት እንደሸመናቸው እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን የዕብራውያንን የሚደጋገም ይዘት እንመልከት፡፡

# የሚደጋገም ይዘት

ባለፈው ትምህርታችን፣ የዕብራውያንን መጽሐፍ ገዢ ዓላማ በዚህ መንገድ ጠቅለል አድርገነው ነበር፡

> ***የዕብራውያን ጸሐፊ መጽሐፉን የጻፈው ተደራሲያኑ በአካባቢያቸው የተስፋፋውን የአይሁድ አስተምህሮ በመቃወም ለኢየሱስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ለመምከር ነው፡፡***

በትምህርታችን በዚህ ነጥብ ላይ፣ ጸሐፊው ተመሳሳይ ጉዳዮችን ደግሞ ደጋግሞ በማንሳት ዓላማውን እንዴት እንዳሳካ ማየት እንፈልጋለን፡፡

በዕብራውያን መጽሐፍ የተደጋገመውን ጭብጥ በቅርበት መመልከታችን ጸሐፊው ሦስት ዋና ጉዳዮችን በመደጋገም ዓላማውን እንዳሳካ ይገለጥልናል፡፡ በመጀመሪያ፣ ታሪክ በኢየሱስ አማካይነት ወደ ፍፃሜው ቀን በመድረሱ ጭብጥ ላይ ትኩረትን ይሰጣል፡፡ ሁለተኛ፣ ለዚህ እምነት ብሉይ ኪዳናዊ ድጋፉን ያቀርባል፡፡ ሦስተኛ፣ ተደራሲያኑ በክርስትና እምነታቸው እንዲፀኑ በርካታ ምክሮችን ያቀርባል፡፡ የመጨረሻው ዘመን በኢየሱስ ስለመምጣቱ በሚናገረው የጸሐፊው እምነት እንጀምር፡፡

# የመጨረሻው ዘመን በኢየሱስ

አብዛኛውን ጊዜ፣ "የመጨረሻው ዘመን" ስለሚባለው መግለጫ የክርስቶስ ተከታዮች ሲሰሙ አዕምሯቸው በቀጥታ የሚነጉደው ክርስቶስ በክብር በሚመለስበት ወቅት ወደሚሆኑት ነገሮች ነው፡፡ አብዛኛዎቻችን ስለ ታላቁ መከራ፣ ስለ ንጥቀት፣ እና ስለ ሺህ ዓመት የተቻለንን ሁሉ ለመረዳት ብዙ ጊዜ እንወስዳለን፡፡ በዕብራውያን መጽሐፍ ስለ "መጨረሻው ዘመን" ስንናገር ግን፣ ከክርስቶስ ዳግም መመለስ ጋር በቀጥታ ከሚያያዙ ክስተቶች የዘለለ ነገር በልቡናችን ይዘን ነው፡፡

ክርስቲያናዊ የነገረ-መለኮት ምሁራኑ ስለ መጨረሻው ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ከ"ነገረ-ፍፃሜ" ጋር ያጣቅሱታል፡፡ ይህ ቃል *eschatos* (ἔσχατος) ከተሰኘው የግሪክ ቃል የተወሰደ ሲሆን ትርጓሜውም "ፍፃሜ" ወይም "መጨረሻ" ማለት ነው፡፡ የሚያስገርመው፣ ይህ የአዲስ ኪዳን ቃል አገባብ በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰው ገና ጥንት በዘዳግም 4፡30 "በዘመኑ ፍፃሜ" ተብሎ ሲጠቀስ ነው፡፡ በዚያ ስፍራ፣ እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ ቢያምፅ ለምርኮ እንደሚሰጥ ሙሴ ያስጠነቅቃል፡፡ ቢመለሱ ግን፣ በዘመን ፍፃሜ፣ ከምርኮ ተሰብስበው ተወዳዳሪ ወደ ሌለው የእግዚአብሔር በረከት ውስጥ እንደሚገቡ ያረጋግጥላቸዋል፡፡ የብሉይ ኪዳን ነቢያትም እስራኤል ከምርኮ ከመመለሷ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ከ"ዘመን ፍፃሜ" ጋር አያይዘውታል፡፡

ዕብራውያን 1፡1-2 ስንመለከት የዕብራውያን ጸሐፊ መጽሐፉን ሲጽፍ በልቡ ነገረ-ፍፃሜን እንደያዘ መመልከት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ እስኪ ገና ከጅማሬው የጻፈውን አድምጡ፡

> ***ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥***
> ***ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤ (ዕብ 1፡1-2)***

እነዚህ የመክፈቻ ጥቅሶች እግዚአብሔር በክርስቶስ "በዚህ ዘመን መጨረሻ" ወይም በኤስካቶሎጂካል "ቀናት" ምን እንዳደረገ እንዴት እንዳጣቀሱ ተመልከቱ፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ ይህንን ሲል ምን ማለቱ ነው? ለእርሱ የነገረ-ፍፃሜ ጉዳይ ለምን ወሳኝ ሆነ?

> **ገና በጽሑፉ መክፈቻ ገፅ፣ በዕብራውያን መጽሐፍ የመጀመሪያ ቁጥሮች ውስጥ፣ ኢየሱስ ከእርሱ አስቀድመው የመጡ የትንቢት ቃሎች ፍፃሜ መሆኑን እንዲያውቁ ይፈልጋል፡፡ "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፤" ይላል፡፡ ያም ማለት ኢየሱስ ከእርሱ አስቀድሞ የመጡ ነገሮች ሁሉ ፍፃሜ ነው ማለት ነው፡፡ እርሱ የጌታ መምጣት፣ የጌታ ቀን መምጣት፣ የመንግሥቱ ጅማሬ፣ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ሊናገር የሚፈልገው የፍፃሜ ቃል ነው፤ ያም በኢየሱስ ውስጥ ይገኛል፡፡ (ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ)**

በዕብራውያን የተገለጠውን ነገረ-ፍፃሜ ለመረዳት፣ በብሉይ ኪዳን ፍፃሜ እና በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሚገኘው በእስራኤል ታሪክ ቀኝ ግራ ፊት ኋላ መጓዝ ይገባናል፡፡ በነገሥታቱ ዘመን፣ እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ እጅግ ጥልቅ በሆነ አመፅ ውስጥ ተዘፍቃ ነበር፡፡ በስተመጨረሻም አብዛኛውን ሰሜናዊው እስራኤል በምርኮ ጠራርጎ ይወስድ ዘንድ የአሦርን ሠራዊት ሰደደባቸው፡፡ ቆይቶም፣ የባቢሎን ሠራዊት በይሁዳ ላይ ተመሳሳዩን እንዲያደርግ እግዚአብሔር ላከው፡፡ እ.አ.አ. በ586 ዓ.ዓ. አካባቢ፣ የእስራኤልና የይሁዳ ቅሬታዎች በመጨረሻዎቹ ቀናት እግዚአብሔር የሚያስተላልፈውን ፍርድና በረከት ተስፋ በማድረግ ወደ ተስፋዪቱ ምድር ተመለሱ፡፡ ሆኖም መጠነ-ሰፊ ንስሓ አልተካሄደም፡፡ በውጤቱም፣ እስራኤል ለአምስት ምዕተ-ዓመታት  በምድያም ፣ በፋርስ፣ በግሪኮች እና በስተመጨረሻም በሮሜ የጭቆና አገዛዝ ስር ወደቀች፡፡

በብሉይና በአዲስ ኪዳን መካከል በሚገኙ ዘመናት፣ አብዛኛው የአይሁድ ማኅበረሰብ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር ፍርድንና በረከትን ያመጣል ብለው በማያወላውል ተስፋ ሲጠብቁ ነበር፡፡ ይህ ተስፋ ለእነርሱ በጣም ወሳኝ ነው ስለዚህም ታሪክን ሁሉ በሁለት ታላላቅ ዘመናት ከፍለዋል፡፡ እስራኤል በኃጢአት የተዘፈቀችበትንና ለምርኮ የተዳረገችበትን ዘመን “የአሁን ዘመን” ይሉታል፡፡ እግዚአብሔር በጠላቶቹ ላይ የመጨረሻውን ፍርድ የሚስተላልፍበትን፣ በታመኑት ህዝቡ ላይ ደግሞ ታላቅ በረከቱን የሚያፈስስበትን ዘመን “የሚመጣው ዘመን” ይሉታል፡፡ በብሉይ ኪዳን ትንቢቶችም መሠረት፣ ከዚህኛው ዘመን ወደሚመጣው ዘመን የሚያሸጋግር የዳዊትን ታላቅ ልጅ፣ መሲሁን እንደሚልክ ያውቃሉ፡፡

የዕብራውያን ጸሐፊም በዘመነ ፍፃሜ ላይ በማትኮር፣ ከተደራሲያኑና ከሰፊው የአይሁድ ማኅበረሰብ ጋር የሚጋራውን እምነት ይገነባል፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ግን፣ በኢየሱስ የሚያምኑና የማያምኑት ጉዳዩን በተለያየ መንገድ እንደሚያዩት ደግሞ ደጋግሞ ያመለክታል፡፡ የማያምኑት አይሁድ መሲሁ ትዕይንታዊና ቅፅበታዊ በሆነ መንገድ በአሁኑ ዘመንና በሚመጣው ዘመን መካከል ሽግግር ያደርጋል ይላሉ፡፡ የኢየሱስተከታዮች ግን ኢየሱስ የመጨረሻውን ዘመን በሦስት እርከኖች እንደሚያመጣው ያውቃሉ፡ በመጀመሪያ ምፅዓቱ መንግሥቱን በይፋ ያውጃል፣ በቤተክርስቲያን ዘመን ደግሞ መሲሃዊ መንግሥቱን ያስፋፋል፣ በክብር ተመልሶ በሚመጣበት ወቅት ደግሞ የመሲሃዊ መንግሥቱ ፍፃሜ ይሆናል፡፡ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍትም የሐዋርያት ሥራ 2፡17 እና 2ኛ ጴጥሮስ 3፡3 በመሳሰሉ ምንባቦች እነዚህን ሦስት እርከኖች “የመጨረሻው ዘመን” በማለት ይጠቅሷቸዋል፡፡

የዚህን ሃሳብ ጠቃሚነት የምትገነዘቡት የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ “መጨረሻው ዘመን” ተመሳሳይ ቋንቋ የከስድስት ያላነሰ ጊዜ የተጠቀመ መሆኑን ስታስተውሉ ነው፡፡ በዕብራውያን 2፡5፣ ክርስቶስ በክብር ስለሚመለስበት ስለ “ሚመጣው ዓለም” ጽፏል፡፡ በ6፡5 ውስጥ ደግሞ አብዛኞቹ ተደራሲያኑ ስላለፉበት ሊመጣ ስላለው የዓለም ኃይል ጽፏል፡፡ በ9፡11 ደግሞ፣ ክርስቶስ “አሁን በዚህ ያሉት መልካም ነገሮች” ምንጭ ስለ መሆኑ ይጠቅሳል፡፡ በ9፡26 ደግሞ፣ የኢየሱስን የምድር አገልግሎት “የዘመን ፍፃሜ” በማለት ይጠቅሰዋል፡፡ በ13፡14 ውስጥ፣ የክርስቶስ ተከታዮችን የመጨረሻ ተስፋ “የምትመጣዋ ከተማ” በማለት ይጠቅሳል፡፡ ስለ እነዚህ ስለ መጨረሻው ዘመን በተደጋጋሚ የተጠቀሱ የታወቁ መንገዶች በጸሐፊው ዓላማ ውስጥ ምን ያህል ወሳኝ ስፍራ እንዳላቸው ቅምሻውን ያሳዩናል፡፡

በዕብራውያን ይዘት ውስጥ የተደጋገሙት መሪ ሃሳቦች በኢየሱስ ስለሚመጣው የመጨረሻ ዘመን ትኩረት ማድረጋቸውን ከተመለከትን፣ በመጽሐፉ ውስጥ ስለተደጋገመው ሁለተኛ ጉዳይ ወደመነጋገሩ እንሸጋገራለን፣ ያም ጸሐፊው ስላነገበው ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት ብሉይ ኪዳናዊ ማረጋገጫ ይሆናል፡፡

## ብሉይ ኪዳናዊ ማረጋገጫ

የዕብራውያን መጽሐፍ፣ ከብሉይ ኪዳን ወደ 100 ለሚጠጉ ጊዜያት ጠቅሷል፣ ወይም አጣቅሷል ወይም አመልክቷል፡፡ እነዚህም የብሉይ ኪዳን ማጣቀሻዎች ለጸሐፊው ዓላማ ወሳኝ ስለነበሩ በመጽሐፉ ወሳኝ ዋና ክፍሎች ውስጥ ደጋግመው ይታያሉ፡፡ ይህ ለምን እንደሆነ መረዳትም አዳጋች አይሆንም፡፡ በአካባቢው የነበረውን የአይሁድ ማኅበረሰብ አስተምህሮ ለመሞገት፣ ሁላቸው ቅዱስ ብለው የሚቆጥሩትን የብሉይ ኪዳን ዶኩሜንት የዕብራውያን ጸሐፊም መረጃው ያደርጋል፡፡

## ጭብጥ ዳራዎች

ለዚህ ትምህርት የያዝነውን ዓላማ ለማሳካት የዕብራውያን ጸሐፊ ደግሞ ደጋግሞ ከብሉይ ኪዳን ያጣቀሰባቸውን እና ያስተናገደባቸውን አምስት መንገዶች መመልከቱ ይጠቅማል፡፡ በመጀመሪያ፣ ወደ ብሉይ ኪዳን ጭብጥ ዳራዎች ትኩረትን ይስባል፡፡

በቀላሉ ለማስቀመጥ፣ ከዕብራውያን መጻሕፍት አንዳንድ ታሪካዊ ዝርዝሮችን በማንሳት ጥቂት ቃላቶችን ይጠቅሳል፡፡ ከዚያም እነዚያን ጭብጦች ስለ ክርስትና እምነት ከሚያቀርበው መልእክት ጋር ያስማማል፡፡ ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 7፡2 ከዘፍጥረት 14፡18 በመጥቀስ፣ "መልከጼዴቅ፣ የሰላም ንጉሥ" የተሰኘው ስም "የጽድቅ" እና "የሰላም ንጉሥ" ማለት ነው በማለት ያብራራል፡፡ ይህም ጭብጥ ዳራው በኢየሱስና በመልከፄዴቅ መካከል የሚያቀርበውን ንፅፅር ያጠናክርለታል፡፡

ሌላ ምሳሌ ለማንሳት፣ በዕብራውያን 12፡20 እና 21 ውስጥ ጸሐፊው፣ በዘፀአት 19፡12፣13 ደግሞም በዘዳግም 9፡19 የተመዘገበውን እና እስራኤላውያን በሲና ተራራ የተገለጠባቸውን ፍርሃት ይዘግባል፡፡ ከዚያም የእስራኤልን ፍራቻ የክርስቶስ ተከታዮች በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ከሚጠብቃቸው ደስታ ጋር ያነጻጽራል፡፡

## ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት

በሁለተኛ ደረጃ፣ ጸሐፊው በእርሱም ዘመን እውነትነት ያላቸውን ብሉይ ኪዳናዊ የነገረ-መለኮት አመለካከቶችን ይጠቅሳል፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች፣ ቀላል ታሪካዊ ጭብጦችን ከመጥቀስ ይልቅ፣ በዕብራውያን ጽሑፎች በተረጋገጡ ነገረ-መለኮታዊ እምነቶች ላይ ያተኩራል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ስለራሱና ስለሌሎች ጉዳዮች የሚያዙ የእምነት አቋሞች ከእግዚአብሔር ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው፡፡

ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 1:5 ውስጥ፣ ጸሐፊው 2ኛ ሳሙኤል 7:14 ወይም ተጓዳኙን 1ኛ ዜና 17:13 ያጣቅሳል፡፡ በዚህ ስፍራ፣ ከዳዊት ዘመን ጀምሮ፣ ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ በጠቅላላ የእግዚአብሔር “ልጅ” ተብሎ እንደሚጠራ እግዚአብሔር ያውጃል፡፡

በዕብራውያን 1:7 ውስጥ፣ መላእክት አገልጋይ መናፍስት ተብለው መገለጣቸውን ከመዝሙር 104:4 ጸሐፊው ይጠቅሳል፡፡

በዕብራውያን 2:6-8፣ መዝሙር 8:4-6 ይጠቅሳል፡፡ የሰው ዘር ከመላእክት የሚያንሰው እስከመፍፃሜዋ ቀን ድረስ ብቻ ነው፣ ምክንያቱም ከክርስቶስ ጋር በፍጥረት ላይ የሚገዙት መላእክት ሳይሆኑ የሰው ዘር ነው በማለት መከራከሪያውን ያቀርባል፡፡

ዕብራውያን 2:13 ኢሳያስ 8:17-18 ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ ጥቅሶች የእግዚአብሔር ነፃ የማውጣት በረከቶች የአብርሃም ዘር ለሆነው ለሰው ልጅ እንጂ ለመላእክት አልተሰጡም፡፡

በዕብራውያን 6:13-14፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን መሃላ ከዘፍጥረት 22:17 ያጣቅሳል፡፡ በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን ቋሚና እስከ አዲስ ኪዳን ዘመን ድረስ ዘላቂ መሆኑን ነን አረጋግጧል፡፡

በዕብራውያን 12:29፣ ጸሐፊው ከዘዳግም 4:24 በመጥቀስ እግዚአብሔር የሚባላ እሳት መሆኑን ገልጧል፡፡ ይህንን ያደረገው እግዚአብሔር ዛሬም በክርስቶስ የሚባላ እሳት ነው የሚለውን ትምህርቱን ለማጠናከር ነው፡፡

በዕብራውያን 4:4-7፤ 8:5፤ 9:20፤ 10:30-31፤ 10:38 እና 13:5 ውስጥ ተመሳሳይ ምሳሌዎች ይታያሉ፡፡ በእነዚህ ምንባቦች ውስጥ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ በብሉይ ኪዳን የተመሠረቱ አንዳንድ ነገረ-መለኮታዊ አመለካከቶች በአዲስ ኪዳን ዘመንም እውነት ሆነው ዘልቀዋል፡፡

> ***የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ ከብሉይ ኪዳን የሚልቅ መሆኑን ቢገልጥም፣ ኢየሱስ ሰላን ብሉይ ኪዳንን አሳንሶ፣ ወይም በቃ ያፈጀ ነው ብሎ ወይም በቀላሉ ቸል ሊባል ይችላል፤ ከዚህ በኋላ ልናነበው አይገባም፤ ብሎ በአንድም ነጥብ እንኳን አልጠቀሰም፡፡ የዚህን ነገር ፍንጭ እንኳን የትም አናገኝም፡፡ በየትኛም ስፍራ የዕብራውያን ጸሐፊ ብሉይ ኪዳንን የእግዚአብሔር ቃልነቱን በመቀበል ፍፁም ከበሬታ በመስጠት ነው የሚጠቅሰው፡፡ ከሁሉ እጅግ ወሳኙ ደግሞ፣ የኢየሱስ ማንነት ትርጉም የሚሰጥ ይሆን ዘንድ ወሳኞቹን ክፍሎች ያዋቀረው ብሉይ ኪዳን መሆኑ ነው፡፡ ኢየሱስ ሊቀ ካህን ነው፡፡ ሊቀካህን ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ምላሹ በብሉይ ኪዳን ተቀምጧል፡፡ የተወሰኑ መስዋዕቶችን ጠቅሷል፡፡ ደም ማለት ምን ማለት ነው? በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ቅድስተ ቅዱሳን ምን ማለት ነው? አዎን፣ ዕብራውያን እንደሚነግረን ሰማያዊ የመገናኛ ድንኳን ነው ሆኖም ግን በምድራዊውም ድንኳንና በሰለሞን መቅደስም ተምሳሊቱ ተቀምጧል፡፡ እንግዲያው በርካቶቹ ክፍሎች፣ የግለሰብ ባህርይን ሁሉ የሚያካትቱት፣ የተመሠረቱት በብሉይ ኪዳኑ የእምነት መለያ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 11 የተጠቀሰው በጎ ምሳሌ ወይም በዕብራውያን 3 መጨረሻ የተጠቀሰውና በምድረበዳ ወድቀው የመቅረታቸው ክፉ ተምሳሊት የተመሠረተው በብሉይ ኪዳን ነው፡፡ እነዚያ ሁሉ ተወሰዱት ከብሉይ ኪዳን ነው፡፡*** ***ዶ/ር ዲ.ኤ. ካርሰን***

## ግብረገባዊ ግዴታዎች

በሦስተኛ ደረጃ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ በተጨማሪም የማይሻሩ የሞራል ግዴታዎችን ይጠቅሳል፡፡ በእነዚህ ጉዳዮች፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ ሞራላዊ ግዴታዎችን አስቀምጧል፡፡ እነዚህ ግዳጆች ለአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ህዝብም መለኪያ ሆነው ዘልቀዋል፡፡

ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 3፡7-15 ውስጥ፣ እስራኤል በእግዚአብሔር ላይ እንዳታምፅ በመዝሙር 95፡7-11 እንዳስተማረ አመልክቷል፡፡

እግዚአብሔር በሚቀጣት ወቅት እስራኤል ተስፋ እንዳትቆርጥ ምሳሌ 3፡11-12 እንዳሳሰበ ዕብራውያን 12፡5-6 ያመለክታል፡፡

ተደራሲያኑ ምሳሌ 4፡26 እንዲጠብቁና የጽድቅን መንገድ አጥብቀው እንዲከተሉ ዕብራውያን 12፡13 መመሪያ ይሰጣል፡፡

በዕብራውያን 13፡6፣ ተደራሲያኑ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን መተማመን እንዲገልጡ፣ ጸሐፊው ውስጥ ከመዝሙር 118፡6-7 በመጥቀስ ያደፋፍራቸዋል፡፡

የብሉይ ኪዳን የሞራል ግዴታዎች በአዲስ ኪዳን የክርስቶስ ተከታዮችም ዘንድ በፅኑ እንደሚቀጥሉ እነዚህ ማጣቀሻዎች ያመለክታሉ፡፡

## የነገረ-ፍፃሜ ትንበያዎች

በአራተኛ ደረጃ፣ በርካታ ነገረ-ፍፃሜያዊ ትንቢቶችን ጸሐፊው ከብሉይ ኪዳን ይጠቅሳል፡፡

የብሉይ ኪዳን ጸሐፍት ስለ “መጨረሻው ዘመን” በበርካታ ምንባቦች ውስጥ ተንብየዋል፡፡ የእስራኤል ግዞተኝነት ሲያከትምና የእግዚአብሔርም ድል አድራጊ መንግሥት በመላው ዓለም ሲስፋፋ እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ጽፈዋል፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊም የእግዚአብሔር የፍፃሜ ፍርድና በረከት በክስቶስ የተፈፀመ መሆኑን ለማሳየት በርካታ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶችን ተጠቅሟል፡፡

ለምሳሌ፣ ዕብራውያን 1፡6 ዘዳግም 32፡43 ን በግሪክኛው የብሉይ ኪዳን ቅጂ በሰብዓ-ሊቃናት፣ እንደተጠቀሰው ዓይነት ጠቅሶታል፡፡ እግዚአብሔር የመጨረሻውን ድል በጠላቶቹ ላይ ሲቀዳጅ መላእክት አንገቶቻቸውን ዝቅ በማድረግ በትህትና እንደሚያመልኩት እነዚህ ጥቅሶች ይናገራሉ፡፡

በተመሳሳይ መንገድ፣ በዕብራውያን 1፡10-12 ውስጥ፣ ጸሐፊው መዝሙር 102፡25-27 ይጠቅሳል፡፡ መላእክት በትልቁ ከበሬታን የሚያገኙበት የአሁኑ የፍጥረት ሥርዓት፣ በታሪክ ፍፃሜ ላይ እንደሚጠፉ ምንባቡ ይተነብያል፡፡

ዕብራውያን 1፡13 ደግሞ የእርሱ ታላቅ ልጅ መሲሁ ከመላእክት እጅግ የከበረ እንደሚሆን ዳዊት የተናገረውን የዓለም አቀፋዊ ሉዓላዊነት ትንቢት ለማመልከት መዝሙር 110፡1 ይጠቅሳል፡፡

በዕብራውያን 5፡6 እና 7፡17፣ ጸሐፊው መዝሙር 110፡4 ይጠቅሳል፡፡ የዳዊት ታላቅ ልጅ ስለሚቀበለው የንግሥና ክህነት የተነገረው ትንት ከራሱ የሚወጣ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተቀበለው መሆኑን አፅንዖት ይሰጠዋል፡፡

በዕብራውያን 8፡8-12፣ ጸሐፊው ከኤርምያስ 31፡31-34 ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ ጥቅሶች፣ እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት መጓዝ ያቃተውን የሰውን ዘር ችግር፣ ከእስራኤል ምርኮ በኋላ፣ አዲሱ ኪዳን እንደሚያስወግደው ይተነብያሉ፡፡

ዕብራውያን 10፡16-17፣ ደግሞ በክርስቶስ የሆነው አዲስ ኪዳን ከዚያ በኋላ መስዋዕትን ለአንድ ጊዜና ለዘላለም በማድረግ እንደሚያስቀረው ለማሳየት ኤርምያስ 31 ደግሞ ይጠቅሳል፡፡

በዕብራውያን 7፡21፤ 10፡37፤ 12፡26 ውስጥም፣ ጸሐፊው ስለመጨረሻው ቀን የተነገሩ ትንቢቶችን ያነሳል፡፡

## ሥርወ-መንግሥታዊ ጭብጦች

በአምስተኛ ደረጃ፣ በመዝሙራት ውስጥ ስለ ዳዊት ዘር የተነገሩ ሥርወ-መንግሥታዊ ጭብጦችን ጸሐፊው ይጠቅሳል፡፡

እነዚህ ምንባቦች የዳዊት ሥርወ-መንግሥት ስለሚጠበቅበት ለእግዚአብሔር የታመነ አገልግሎት የመስጠት ስታንዳርድ ይናገራሉ፡፡ ሆኖም፣ የብሉይ ኪዳኖቹ የዳዊት ዝርያዎች እነዚህን ስታንዳርዶች በፍፅምና አልጠበቁም፡፡ ስለዚህ ከዳዊት ቤት የሆነውን ይህንን ስታንዳርድ የፈፀመ ሉዓላዊና ፍፁም ዘር ኢየሱስ መሆኑን የዕብራውያን ጸሐፊ ይናገራል፡፡

ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 1፡5፣ ጸሐፊው መዝሙር 2፡7 እና 2ኛ ሳሙኤል 7፡14 ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ ጥቅሶች መንግሥታትን ሁሉ ይገዛ ዘንድ ከዳዊት ዘር የሆነውን ልጁን እንደሚያስነሳ ያመለክታሉ፡፡

ዕብራውያን 1፡8-9፣ መዝሙር 45፡6-7 ይጠቅሳል፡፡ ይህ የንጉሣዊ ሠርግ ዝማሬ ጽድቅን የሚወድደውንና አመፅን የሚጠላውን ከዳዊት ወገን የሆነውን ሥርወ-መንግሥት በማክበር እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚገዛ ያሳያል፡፡

በዕብራውያን 2፡11-12፣ ጸሐፊው መዝሙር 22፡22 ይጠቅሳል፡፡ በዚህ ጥቅስ፣ ዳዊት የድሉን ደስታ ከሌሎች እስራኤላውያን ጋር እንዲካፈል ይጠየቃል፡፡ ኢየሱስም ድሉን ከአብርሃም ልጆች ጋር በመካፈል ይህንን ሥርወ-መንግሥታዊ ጭብጥ እንደፈፀመ ጸሐፊው እነዚህ ጥቅሶች በመጠቀም ያሳየናል፡፡

በዕብራውያን 10፡5-7፣ ጸሐፊው መዝሙር 4-፡6-8 ይጠቅሳል፡፡ በእነዚህ ጥቅሶች፣ ዳዊት ከእንስሳት መስዋዕት ይልቅ ሰውነቱን ለእግዚአብሔር እንዲያቀርብ ይጠየቃል፡፡ ጸሐፊውም ይህን ኢየሱስ በመስቀል ላይ ራሱን መሰዋቱ ሉዓላዊ እና የነገረ-ፍፃሜያዊ ትንቢት ምልዓት ከመሆኑ ጋር ያዛምደዋል፡፡

እስካሁን ድረስ በዕብራውያን መጽሐፍ የተዘረዘሩትንና በነገረ-ፍፃሜ ከክርስቶስ ጋር የተያያዙትን ደግሞም የጸሐፊውን ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት የሚደግፉ የብሉይ ኪዳን ማረጋገጫዎችን ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ ጸሐፊው ስለመጽናት ያቀረበውን ማሳሰቢያ የሚጠቅሰውን ሦስተኛውን ድግግሞሽ እንመለከታለን፡፡

## ስለ መጽናት የተሰጠ ምክር

> ***ወደ ዕብራውያን ሰዎች የተጻፈው ደብዳቤ ጸሐፊ አድማጮቹ በእምነት እንዲፀኑ በበርካታ መንገዶች ያሳስባል፡፡ በዚህ የመጨረሻ ዘመን፣ ልጁን በመላክ በእነርሱ የጀመረውን ዓላማውን ለመፈፀም እግዚአብሔር በሥራ ላይ እንደሆነ የሚያመለክቱ በርካታ ጥቅሶችን ከብሉይ ኪዳን ይጠቅሳል፡፡ በተለይም በምዕራፍ 11 በመከራ ውስጥ በእምነታቸው ፀንተው እንዳለፉ የተጠቀሱት አባቶች፣ የፅናት ታላቅ ተምሳሊቶች ሆነው ተጠቅሰዋል፡፡ በተለይ ክርስቶስ ራሱ "ነውርን ንቆ፣ በፊቱም ስላለው ክብር በመስቀል ታግሦ" ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ ይህም በዚህ ዘመን የሚኖሩ ክርስቲያኖች ሊከተሉት የሚገባ ተምሳሊት ነው፡፡*** *(ዶ/ር ሲሞን ቫይበርት)*

በቀደመው ትምህርታችን፣ የእብራውያን ጸሐፊ በምዕራፍ 13፡22 ውስጥ "የምክር ቃል" በማለት አጠቃላይ መፅሐፉን እንደገለጠው ጠቅሰናል፡፡ በትክክል ቆጥራችሁ ከሆነ፣ ዕብራውያን ወደ 30 የሚጠጉ የምክር ቃሎችን አካትቷል፡፡ ወደፊት እንደምንመለከተው፣ እያንዳንዱ ምክር አንድን ጉዳይ የሚዳስስ ሲሆን፣ በጥቅሉ ግን ሁሉም ቀደምት ተደራሲያኑ ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ጥሪ እንዲያስተላልፉ ተደርገው የተቀረፁ ናቸው፡፡

በትምህርታችን በዚህኛው ነጥብ ላይ፣ ጸሐፊው ስለመፅናት የሰጣቸውን ሁለት ወሳኝ ምክሮች እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ጸሐፊው ከተደራሲያኑ ስለሚጠብቀው ምላሽ ጥቂት ሃሳብ እንሰነዝራለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ተደራሲያኑን እንዲፀኑ እንዴት እንዳነሳሳቸው እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን ጸሐፊው ሊያይ የሚፈልገውን ምላሽ መጠን እንመልከት፡፡

## ምላሾች

ሊጠቀሱ ከሚገባቸው የእብራውያን መጽሐፍ ገፅታዎች አንዱ ጸሀፊው ከተደራሲያኑ የሚጠብቀው ምላሽ መጠነ ልክ ነው፡፡ እንግዲህ ጥንታዊ ቋንቋዎችን ማለትም የአዲስ ኪዳኑን ዘመን የግሪክኛ ቋንቋ ዓይነት ስናነሳ፣ ለእያንዳንዷ መግለጫ ትርጓሜ ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ ስለዚህ፣ በጥቂት ግልፅ ምሳሌዎች ላይ ብቻ እናተኩራለን፡፡ በጥቅሉ፣ ተደራሲያኑ መጽሐፉን በስሜት፣ በጭብጥና በባህርይ ረገድ እንዲያዘምዱለት ጸሐፊው ያበረታታቸዋል፡፡ ቀደምት ተደራሲያኑ መፅናት ይችሉ ዘንድ፣ ለእነዚህ ምላሾች መጠነ ልክ ትኩረት ሊሰጡ ይገባቸዋል፡፡

በመጀመሪያ፣ ጸሐፊው ተደራሲያኑን የሚመክረው ስለ እምነታቸው ስሜታዊ መገለጫዎች ጉዳይ ነው፡፡ በዕብራውያን 3፡8፣15፣ "ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ" ይላቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ምዕራፍ ቁጥር 13 ውስጥ፣ "… ከእናንተ ማንም እልከኛ እንዳይሆን፣ …. በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ" ይላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በ4፡1 ውስጥ "እንጠንቀቅ" ይላል ወይም ቃል በቃል ስናስቀምጠው፣ በተለይም በዚህ አውድ "ወደ ዕረፍቱ ሳንገባ እንዳንቀር እንፍራ" ይላል፡፡ ስለዚህም ተደራሲያኑን በ4፡16 ውስጥ "በእምነት እንቅረብ" በማለት ወደ ጸጋው ዙፋን ለእረዳታ እንዲቀርቡ

ያበረታታቸዋል፡፡ በ10፡22 ደግሞ፣ “በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ” ይላቸዋል፡፡ በ10፡35፣ “ድፍረታችሁን አትጣሉ” በማለት ይመክራቸዋል፡፡

ለዕብራውያን ጸሐፊ ስሜት ነክ የሆኑት ጉዳዮች ወሳኝ የሆኑትን ያህል፣ ተደራሲያኑ ከጭብጥም ረገድ ጽሑፉን እንዲያዛምዱለት ስለሚሻ በዚያም ረገድ ይመክራቸዋል፡፡ ከእግዚአብሔር የተቀበላቸው መልእክቶቹ ነገረ-መለኮታዊ አስተምህሯቸውንና የእምነት አቋማቸውን እንዲያቀኑ ይፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፣ በእብረውያን 2፡1 “ስለ ሰማነው ነገር አብልጠን እንጠንቀቅ” ይላቸዋል፡፡ በ3፡1፣ “ክርስቶስን ተመልከቱ” በማለት ያሳስባቸዋል፡፡ በ6፡1 ደግሞ፣ “ስለ ክርስቶስ መጀመሪያ የሚነገረውን በመተው” በመረዳታቸው እያደጉ እንዲሄዱ ያሳስባቸዋል፡፡

ማራኪ በሆነ መንገድ፣ በመጀመሪያ አካባቢ ስለ ባህርያዊ መለጫዎች ፀሐፊው ጫን ብሎ አልጠቀሰም፡፡ እርግጥ ነው፣ ምክሮች አብዛኛውን ጊዜ ባህርያዊ እንድምታዎች አሏቸው፣ ሆኖም ባህርይ ነክ ምክሮቹ በግልፅ የተቀመጡት በመጽሐፉ ማብቂያ አካባቢ ነው፡፡ በዕብራውያን 12፡16፣ “ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይገኝ” በማለት ያስጠነቅቃል፡፡ በ13፡1-19፣ እንግዳ ስለመቀበል፣ ስለትዳር፣ የክርስቶስን ስም ስለመጥራትና በጎ ስለማድረግ ይመክራቸዋል፡፡

እነዚህ ምክሮች የዕብራውያን ፀሐፊ ተደራሲያኑ ለመጽሐፉ እንዲሰጡት የሚፈልገውን ምላሽ በብዙ መንገዶች ያስረዳሉ፡፡ ለክርስቶስ የታመነ አገልግሎት ለመስጠት ይችሉ ዘንድ በስሜት፣ በሃሳብና በባህርይ ረገድ ግንዛቤ ሊኖራቸው እንደሚገባ በግልፅ ያሳስባሉ፡፡

የዕብራውያን ጸሐፊ ምክሮች በርካታ ምላሾችን እንደሚጠብቁ ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ ስለ መጽናት አሉታዊና አዎንታዊ ተነሳስቶዎችን ጸሐፊው እንዴት እንዳቀረባቸው እንመልከት፡፡

## ተነሳስቶዎች

በአንድ በኩል፣ ጸሐፊው አብዛኞቹን ምክሮቹን በቅርበት የሚያቆራኘው ከአዎንታዊ ተነሳስቶዎች ጋር ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 4፡13-16፣ ጸጋንና እርዳታን ከክርስቶስ ስለመቀበል ይጠቅሳል፡፡ በ13፡16፣ አንዳንድ ድርጊቶች እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኙ በማገለጥ ተደራሲያኑን ያበረታታል፡፡ ጸሐፊው ደግሞ ደጋግሞ የሚያነሳው ደግሞ፣ ዘላለማዊ ብድራት የተቀደሰ ሕይወት ለመኖር የሚያነሳሳ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡ በዕብራውያን 10፡35፣ እንዲህ ይላል፡

> *ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ(ዕብራውያን 10፡35)*

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ተደራሲያኑን ለመምከር፣ አሉታዊ ተነሳስቶዎችንም ይጠቅሳል፡፡ እነዚህ ምክሮች በተቀዳሚነት ስለመለኮታዊ ፍርድ የሚያስጠነቅቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 2፡2-3፣ መላእክትን ያልታዘዙ መቀጣታቸውን ያወሳል፡፡ ታዲያ፣ በክርስቶስ የተገለጠውን መዳን ወንጌል ያከፋፉ ከእግዚአብሔር ፍርድ እንዴት ያመልጣል? በ6፡4-8 ወደ ኋላ የሚንሸራተት ሰው “የተረገመ  የመሆን አደጋ” ውስጥ እንደሆነ ያስጠነቅቃል፡፡ በ10፡26-31 የእግዚአብሔርን ጠላቶችና ተቃዋሚዎችን ሊበላ ስላለው የሚያስፈራ የእሳት ፍርድ ያስጠነቅቃል፡፡

> **ከዕብራውያን መጽሐፍ ዐቢይ መሪ ሃሳቦች አንዱ የመጽናት አስፈላጊ ነው፡፡ ተደራሲያኑ በጽናት እንዲቆሙ፣ በጽናት እንዲገፉ፣ እንዳያፈገፍጉ ያሰሰበበትን፣ ደግሞም በክርስትና ሕይወታቸው እንዲገሰግሱ በብርቱ የሰበከበትን ሃሳብ ወደ ጎን ትታችሁ የዕብራውያንን መጽሐፍ ማንበብ አትችሉም፡፡ ታዲያ፣ ያንን እንዴት ነው የገለጠው? እኔ እንደማስበው እርሱ ያደረገው ማበረታቻዎችን ከማስጠንቀቂያዎቹ ጋር አመጣጥኖ ማቅረብ ሲሆን፣ ይህም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ እንደሚባለው ዓይነት ነው፡፡ ከማበረታታት አንፃር፣ የዕብራውያን መጽሐፍ በክርስቶስ እና በብሉይ ኪዳን ገፀ-ባህርያት፣ ህዝቦች እና ቃል ኪዳናት መካከል ታዋቂ ንፅፅሮችን ደግሞ ደጋግሞ፣ በመዘገብ ይታወቃል፡፡ እርሱ ከሙሴ ይበልጣል፤ የላቀ ዕረፍት አስገኝቷል፤ እርሱ ከሁሉ ታላቁ ሊቀ ካህን ነው፤ የእርሱ መስዋዕትነት አምሳያ የለውም የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ እውን ነው፣ የዚህ ግልባጩ፣ ማስጠንቀቂያም አለበት፡፡ በዕብራውያን መጽሐፍ የተጠቀሱት ማስጠንቀቂያዎች ዓላማቸው ክርስቲያን ተደራሲያንን ለማንቃትና "እርሱ የክብር ጌታ ሆኖ ሳለ፣ ከነሙሉ ውበቱና ክብሩ ታላቁ ሊቀ ካህን ሆኖ ተሰጥቶኝ ሳለ፣ ባልፀና፣ ዐይኔን ከክርስቶስ ላይ ባነሳ፣ ከእርሱ ጋር መጓዜን በቋርጥ እና እርሱን መመልከቴን ባቆምስ?" የሚለውን እንዲጠይቁ ለማስቻል እና ከእርሱ ውጪ ድነት የሌለ መሆኑን ማመልከት ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም አዎንታዊ ማበረታቻ የሚሰጡ ሲሆን፣ ለእኛ ደግሞ የእምነታችንን ጀማሪና ፍፁም አድራጊ ኢየሱስ ክርስቶስን በመመልከት ሩጫችንን በፅናት ልንሮጥ እንደሚገባ አሉታዊ ቃና ያለውን ማጠንከሪያ በመስጠት ያሳስቡናል፡፡ (ዶ/ር ስቴፋን ጄ.ዌሉም)**

የዕብራውያን ተደራሲያን ስለሚጠብቃቸው ፍርድ የተነገረው ቃል ተርጓሚዎችን ሲያስቸግራቸው ቆይቷል ምክንያቱም አቀማመጣቸው እውነተኛ አማኞች ድነታቸውን ሊያጡ ይችላሉ የሚሉ ስለሚመስሉ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት፣ ክርስቲያኖች በእነዚያ ጉዳዮች ላይ አንዱ በአንዱ ሌላው በሌላኛው ጎን በመሰለፋቸው ምክንያት በዕብራውያን የተቀመጡት ክፍሎች የውጊያ አውድማዎቻቸው ሆነው ሰንብተዋል፡፡ ሁሉን ነገረ-መለኮታዊ ጉዳይ በዝርዝር ለመመልከት ጊዜ ስለማይፈቅድልን ባንሞክርም፣ በእነዚህ ጉዳዮች ሁለት ገፅታዎች ላይ ሃሳብ እንሰነዝራለን፡፡

በመጀመሪያ፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ቴክኒካዊ ስልታዊ መለኮት እንዳልሆነ በልቡናችን ልናደርግ ይገባል፡፡ ይህን ስንል፣ ቅዱሳት መጻሕፍት አንዳንድ ቃሎችን ማለትም ድነትን እንኳን ሳይቀር ሲጠቅሱ ክርስቲያናዊ የነገረ-መለኮት ሊቃውንትና ነገረ-መለኮታዊ ትውፊቶች ከሚጠቅሱት በላቀ መንገድ የተለያዩ አማራጮችን ይጠቀማሉ፡፡ እንዲያውም፣ አንዳንድ ቤተክርስቲያናት አንዳንድ ነገረ-መለኮታዊ ቃላትን የሚጠቀሙት በቅዱሳት መጻሕፍት ከተጠቀሱበት እጅግ አጥብበው ነው፡፡ ምንም ዓይነት ነገረ-መለኮታዊ ግራ መጋባት ሊኖርብን አይገባም የሚል ገራገርነት የወለደው ተስፋ ከቋጠርን፣ እንዚህ ችግሮች ሳይወገዱ ይዘልቃሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ይህ አቀራረብ የእኛን ጠባብ ትርጓሜ ወደ መጽሐፉ ውስጥ በግድ በማስገባት ወደ ማንበብ አደጋ ውስጥ ስለሚከትተን አደገኛ ነው፡፡ ይህ አደጋ በግልፅ የሚታየን የዕብራውያን ጸሐፊ ሃይማኖታቸውን የካዱትን ወይም ከክርስቶስ የኮበለሉትን የገለጠበትን መንገድ በውል ስንገነዘብ ነው፡፡

በአንድ ወገን፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ከሃዲዎችን "ጸድቀዋል" ብሎ አንድም ቦታ ያልጠቀሰ መሆኑን ልብ ማለት ይጠቅማል፡፡ በአዲስ ኪዳን፣ ይህ ቃል ለእውነተኛ አማኞች ብቻ የተቀመጠ ነው፡፡ በሌላ ጎን ደግሞ፣ ምንም እንኳን በሌሎች የአዲስ ኪዳን ክፍሎች ባይተቀስም ወንጌላውያን

ለእውነተኛ አማኞች ብቻ የሚጠቀሙባቸውን አባባሎች የዕብራውያን ጸሐፊም ተጠቅሟል፡፡ ለምሳሌ፣ በዕብራውያን 6፡4-6 ውስጥ፣ ጸሐፊው እንዲህ ያስጠነቅቃል፡

> ***አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን***
> ***መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና። (ዕብራውያን 6፡4-6)***

በዚህ ስፍራ የሚገጥመን ፈታኝ ነገር አብዛኞቻችን ይህንንና ተመሳሳይ መግለጫዎችን በነገረ-መለኮታዊ መዝገበ ቃላታችን የምንጠቀመው እውነተኛ አማኞችን ለመግለጥ ብቻ መሆኑ ነው፡፡ ዕብራውያን 10፡29 ጨምሮ ሌሎችም ምንባቦች ከሃዲዎች በኪዳኑ ደም "የተቀደሱ" ተብለው ተገልጠዋል፡፡ ወይም በ10፡32 ውስጥ "ብርሃን የበራላቸው" ተብለዋል፡፡

በገሃዱ እውነታ፣ በአዲስ ኪዳን የነገረ-መለኮቱ ሊቃውንት "የምትታየዋ ቤተክርስቲያን" በማለት ደጋግመው በሚጠሯት ውስጥ ለሚሳተፉ ይህ መግለጫ አገልግሎት ላይ ውሎ እንመለከታለን፡፡ ይህም "ከማትታየዋ ቤተክርስቲያን" ወይም የእውነተኛ አማኞች አካል ከምትባለው ፈጽሞ የተለየ ነው፡፡ በምትታየዋ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ህዝቦች በውጫዊ መልክ የቤተክርስቲያን አካል ናቸው እንጂ የግድ የውስጣዊ አካሏ ክፍሎች ናቸው ማለት አይደለም፡፡ ይህ መለያ በሮሜ 2፡28-29 አይሁድን ውጫዊ ብቻ በግሪክኛው — *phaneros* (φανερός) ማለትም በውጫዊ አካል በመገረዝ ብቻ አይሁድ የሆኑና ውስጣዊ በግሪክኛው — *kruptos* (κρυπτός) በልባቸው በመገረዝ አይሁድ የሆኑትን ለመግለጥ ከተጠቀመበት ጋር ይመሳሰላል፡፡

ሁለተኛ፣ ከሃዲዎችን የሚጠብቃቸው መለኮታዊ ፍርድ ለአይሁድ የተለየ እንደማይሆን ዘወትር ማስታወስ ይገባናል፡፡ ለምሳሌ፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡1-13 እና 2ኛ ጴጥሮስ 2፡21-22 በመሳሰሉ ምንባቦችም ተመሳሳይ ማስጠንቀቂያዎችን እንመለከታለን፡፡ በጥቅሉ፣ ለድነት በሚያበቃ እምነት በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች እስከ መጨሻው መጽናት እንደሚገባቸው አዲስ ኪዳን ያስተምረናል፡፡ ክርስቶስን ፈፅመው የሚክዱ ግን እምነታቸው ለድነት የሚያበቃ አለመሆኑን ራሳቸው አሳይተዋል ማለት ነው፡፡ ይልቁኑ፣ እምነታቸው የነገረ-መለኮቱ ምሁራን ዳግመው እንደሚጠሩት "ጊዜያዊ" ወይም "የግብዝነት እምነት" ነው፡፡ በ1ኛ ዮሐንስ 2፡19 ስለ ከሃዲዎች እንደተነገረው፡-

> ***ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ ይገለጡ ዘንድ ወጡ። (1ኛ ዮሐ 2፡19)***

በየትኛውም ዘመን ማንም ሰው ከክርስትና እምነት ዘወር ካለ፣ የማትታየዋ ቤተክርስቲያን አካል አለመሆኑን በራሱ መስክሯል ማለት ነው፡፡

**በዕብራውያን መጽሐፍ ምንባቦች ውስጥ አምስት ማስጠንቀቂያዎች ተቀምጠዋል፡፡ አብዛኞቻችን ብንከራከርባቸውም አምስቱም ያዘሉት አንድ ነጥብ መሆኑን ደምድመናል፣ እና አምስቱም አንድ ዐቢይ ዓላማ ያነገቡ መሆናቸውን በማመን በብዙ ቁጥር ልንጠቀምባቸው ይገባል፡፡ ከመጋቢነት አገልግሎትም አንፃር ዓላማቸው ግልፅ ነው፡፡ መጋቢ፣ በማኅበረ**

**ምዕመኑ ያለ እያንዳንዱ ሰው በፅናት ክርስቶስን እንዲከተል ይፈልጋል። እንግዲያው ልናሰምርባቸው የሚገቡ በርካታ ነጥቦች ይኖራሉ ማለት ነው። ማስጠንቀቂያዎች እውነተኛ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው። ለማስመሰል የቀረቡ አይደሉም። የማታለያ የቃላት ጋጋታዎችም አይደሉም። አንድ መጋቢ እሁድ ማለዳ ለማኅበረ ምዕመኑ እንደሚገልጠው አይነት በግልጥ የተነገሩ ማስጠንቀቂያዎች ናቸው። መጋቢው ግን ሁሉን አዋቂ አይደለም። በምኅበረ ምእመኑ የተገኘ ሰው ነፍስ ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል አያውቅም። ክርስቶስን እናምናለን ብለው መናገራቸውን ያውቃል፣ እንደ አዲስ ኪዳን ነገረ-መለኮት ግን እውነታውን የሚገልጠው ጊዜ ነው። ማለቴም፣ በ1ኛ ዮሐንስ ምሳሌውን እንዳየነው፣ የካዱ ሰዎች፣ የአማኞችን ኅብረት የካዱ ሰዎች፣ ወደ ውጪ ሲወጡ፣ ቀድሞውኑም ከእኛ ወገን እንዳልነበሩ አረጋገጡ ማለት ነው፤ ዮሐንስ ለትንሿ እስያ መጻፉን ልብ ይሏል። እናም፣ በዚህም በዕብራውያን እንደምንመለከተው በክርስቶስ እናምናለን ለሚሉት በእውነት ግን የሚያውቁት መሆናቸውን ጊዜ ብቻ ሊገልጠው ለሚችለው ሰዎች ይጽፋል። ዶ/ር ቤሬ ጆስሊን**

*ስለ ዕብራውያን መጽሐፍ አወቃቀርና ይዘት በተመለከትነው ትምህርታችን፣ የመጽሐፉን ሦስት በተደጋጋሚ የተነሱ ይዘቶች አይተናል። አሁን ደግሞ ወደ ሁለተኛው ዐቢይ ነጥባችን ማለትም ወደ አሳማኙ አወቃቀር እንሸጋገራለን።*

# አሳማኝ አወቃቀር

ቀደም ባሉት ትምህርቶቻችን እንደተመለከትነው፣ የዕብራውያን መጽሐፍ ቀደምት ተደራሲያን በመከራ ውስጥ እያለፉ ነበር፡፡ በአቅራቢያቸው ያለውን የአይሁድ ማኅበረሰብ የሃሰት አስተምህሮ የመቀበሉ ፈተና ተስፋፍቶ ነበር፡፡ ስለዚህም የዕብራውያን ጸሐፊ በፍፁም እጅ እንዳይሰጡና በእነዚህ የስህተት አስተምህሮዎች ምክንያት ከክርስቶስ ዘወር እንዳይሉ ሊያሳስባቸው ይጽፋል፡፡ ታዲያ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ይህንን ዓላማውን ለማሳካት የመጽሐፉን ይዘት እንዴት አዋቀረው? ይህስ አሳማኝ አወቃቀር ምን መልክ አለው?

ይህንን የዕብራውያን አሳማኝ አወቃቀር በብዙ ደረጃዎች ልንመለከተው እንችላለን፣ ለአሁኑ ዓላማችን ግን፣ የመጽሐፉን አምስት ዐቢይ አንጓዎች እንመለከታለን፡፡ እነዚህ አምስት አንጓዎች ተደራሲያኑ ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ጸሐፊው እንዴት ሊያሳስባቸው ጥረት እንዳደረገ እንድንመለከት ያስችሉናል፡፡

- የመጀመሪያው ዐቢይ አንጓ ስለ መላዕክት መገለጥ ባለው አመለካከት ላይ የሚያተኩረው በ1፡1-2፡18 የሚኘው ነው፡፡
- ሁለተኛው ዐቢይ አንጓ በሙሴ ሥልጣን ላይ የሚያተኩረው በ3፡1-4፡13 የሚገኘው ነው፡፡
- ሦስተኛው ዐቢይ አንጓ ስለ መልከጼዴቅ የንጉሥ ካህንነት የሚያወሳው በ4፡14-7፡28 የሚገኘው ነው፡፡
- አራተኛው ዐቢይ አንጓ በአዲሱ ኪዳን ላይ የሚያተኩረው በ8፡1-11፡40 የሚገኘው ነው፡፡
- አምስተኛው ዐቢይ አንጓ ስለ ተግባራዊ ፅናት የሚያወሳው በ12፡1-13፡25 የሚገኘው ነው፡፡

## የመላእክት መገለጥ

የዕብራውያን ጸሐፊ አምስቱንም ዐቢይ አንጓዎች የተጠቀመው ተደራሲያኑ በመከራም ውስጥ እንኳን ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው መዝለቅ እንደሚገባቸው ለማሳሰብ ነው፡፡ አስቀድመን በ1፡1-2፡18 መጽሐፉ ስለ መላእክት መገለጥ እንዴት እንደጠቀሰ እንመልከት፡፡

ቀደም ባሉት ትምህርቶቻችን እንደገለጥነው፣ ከቁምራን የተገኙ የአይሁድ ጽሑፎችና የኤፌሶንና የቆላስያስ መጻሕፍትም ጭምር እንዳሳዩን በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ አይሁድ መላእክትን እንደ ኃያል፣ የከበሩ ደግሞም ለአናሳዎቹ የሰው ዘሮች መለኮታዊ መገለጥን እንደሚያመጡ ፍጥረታት ከፍ አድርገው ይመለከቱ ነበር፡፡

በአካባቢው የነበሩ የአይሁድ ማኅበረሰብ ትምህርቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መቆናጠጫ የነበራቸው ሲሆኑ ግን ለመላእክት ከልክ ያለፈ ክብር ይሰጡ ነበር፡፡ ይህም ለመላእክት የሚሰጥ የተጋነነ አክብሮት ክርስቶስን ለሚከተሉ ብርቱ ፈተና ሆኖ ነበር፡፡ እንዲያውም እኮ፣ ኢየሱስ ኢየሱስ ሥጋና ደም ያለው የሰው ዘር መሆኑን ሁሉ ያውቃል፡፡ ታዲያ እንዴት አንድ ሰው ከመላእክቱ መገለጥ ይልቅ የእርሱን ንግግሮች ሊከተል ይችላል?

የዕብራውያን ጸሀፊ ለእነዚህ ተግዳሮቶች ምላሽ የሰጠው በአምስት እርከኖች ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ በዕብራ1፡1-4 ተደራሲያኑ ኢየሱስን መከተል ያለባቸው ኢየሱስ የእግዚአብሔር መለኮታዊ መገለጥ ወደር የለሽ ምንጭ ስለሆነ ሊያመለክታቸው ጽፏል፡፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር በመላእክትና በልዩ ልዩ መንገዶች መናገሩን ጸሐፊው እውቅና ይሰጣል፡፡ ሆኖም፣ በመጨረሻው ዘመን ንጉሣዊ ሊቀካህን ሆኖ ከመለኮት የተላከው ኢየሱስ፣ በመላእክት ከተሰጠው መገለጥ እጅግ የሚበልጥን መገለጥ ገልጦልናል በማለት ማሳመኛውን ያቀርባል፡፡

በ1፡5-14፣ ኢየሱስ ከመላእክት ይበልጣል ምክንያቱም እርሱ ብቸኛው የእግዚአብሔር ልጅ መሲሁ ነው በማለት የዕብራውያን ጸሐፊ ያብራራል፡፡ ኢየሱስ ለዳዊት ቤት የተነገረውን መፈፀሙን ይጠቅሳል፡፡ በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ መሲሁ የእግዚአብሔር ልጅ ድል እንደሚቀዳጅ ለዳዊት የተነገረውንም ትንቢት ኢየሱስ ፈጽሟል፡፡ በንፅፅሩ ደግሞ፣ መላእክት በክርስቶስ ድነትን የሚወርሱትን ለማልገል የሚላኩ መናፍስት ብቻ መሆናቸውን ይጠቅሳል፡፡

በ2፡1-4፣ ተደራሲያኑ በኢየሱስ ለታወጀው ታላቅ የድነት መልእክት ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት እንዲያደርጉ ጸሐፊው ያሳስባል፡፡ በመላእክት የተላለፈውን መልእክት በተላለፉት ላይ የእግዚአብሔር ቅጣት እንዳረፈባቸው ያሳስባቸዋል፡፡ እናም፣ የእርሱ አንባቢዎች መዳናችን በሆነው በክርስቶስ የተገለጠውን መዳን ቸል ቢሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ ሊያመልጡ እንደማይችሉ ያሳስባል፡፡

ዕብራውያን 2፡5-9 ኢየሱስ አሁን የመላእክትም ገዢ መሆኑን በማብራራት የክርስቶስን ሉዓላዊነት ያፀናል፡፡ ወደፊትም አማኞች በጠቅላላ ከእርሱ ጋር በመሆን በእነርሱ ላይ ይነግሣሉ፡፡ እግዚአብሔር ለጥቂት ጊዜ የሰውን ልጅ ከመላእክት ጥቂት እንዳሳነሰው ጸሐፊው ይጠቅስና፣ በሚመጣው ዓለም ግን የሰው ዘር በፍጥረተ ዓለሙ ላይ እንደሚገዛ ያመለክታል፡፡ ይህ ለሰው ዘር የተሰጠ የፍፃሜ ክብር ክርስቶስ አሁን በሰማያት እንደ ንጉሣዊ ሊቀካህን በነገሠበት ንግሥና ውስጥ ይታያል፡፡

በመጨረሻም፣ በዕብራውያን 2፡10-18፣ ኢየሱስ የአብርሃም ዘር መሆኑን ጸሐፊው ይጠቅሳል፡፡ እናም ኢየሱስ የክብሩ ተካፋይ የሚያደርገው የአብርሃምን ዘር እንጂ መላእክትን አይደለም፡፡ ጸሐፊው በዚህ ክፍል ኢየሱስ ከአብርሃም ዘር ጋር ያለውን ትስስር ለማሳየት ዳዊትንና ኢሳያስን ይጠቅሳል፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ፣ በሰው ልጅነቱ፣ የወደቀውን ታላቅ መልአክ፣ የዲያቢሎስን ኃይል መስበሩን ፀሐፊው ይጠቅሳል፡፡ ይህም መለእክትን ነፃ ለማውጣት ሳይሆን፣ የአብርሃምን ወገን ሞት ፍርሃት ነፃ ለማድረግ ነው፡፡ የክርስቶስ የሰው ዘርነት የህዝቡን ኃጢአት የሚያስተሰርይ መሃሪና የታመነ ሊቀ ካህን እንዲሆን አድርጎታል፡፡

# የሙሴ ሥልጣን 3፥1-4፥13

የዕብራውያን ጸሐፊ ከአይሁዱ የመላእክት አስተምህሮ ጋር እንዴት እንደተፋለመ ከተመለከትን፣ ወደ መጽሐፉ ሁለተኛ ዐቢይ አንጓ መሸጋገር ይገባናል፡፡ በዕብራውያን 3፡1-4-13 ድረስ፣ ከሙሴ ሥልጣን ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ተግዳሮቶች ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በእስራኤል ውስጥ የሙሴን ያህል የሚከበር የሰው ዘር የለም፡፡

ለሙሴ ከተሰጠው ከዚህ ከበሬታ የተነሳ፣ በእነዚህ የአይሁድ አስተማሪች አስተምህሮ ብዙም መደነቅ የለብንም፡፡ ለክርስቶስ የሚገባውን ክብር ሳይሰጡ እግዚአብሔር በሙሴ በኩል የገለጣቸውን ሁሉ ሊታዘዙ እንደሚገባ የዕብራውያንን ተደራሲያን ይፈታተኑ ነበር፡፡ በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ለሙሴም የሚገባውን ክብር ይሰጣል፡፡ ግን ሙሴ ምንም እንኳን የእግዚአብሔር የታመነ መልእክተኛ ቢሆንም፣ ኢየሱስ ግን በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ንጉሣዊ ሊቀካህን ስለሆነ እጅግ ይበልጣል፡፡

ይህኛው የመጽሐፉ አንጓ በሦስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፣ እያንዳንዱም የኢየሱስ ሥልጣን ከሙሴ ሥልጣን እንደሚበልጥ የሚናገር ቢያንስ አንድ ማሳሰቢያ ይዟል፡፡ በዕብራውያን 3፡1-6 የሚኘው የመጀመሪያ ክፍል፣ ተደራሲያኑ ኢየሱስን ከሙሴ ይልቅ እንዲያከብሩ ግልፅ ጥሪ ያቀርብላቸዋል፡፡ ሙሴ የእግዚአብሔርን ቤት፣ የመገናኛውን ድንኳን እንደሠራ ይህ ክፍል ያመለክታል፡፡ ኢየሱስ ግን፣ እንደ ንጉሥ ልጅ፣ በእግዚአብሔር ቤት በቤተክርስቲያን ላይ ይገዛል፡፡

በዕብራውያን 3፡1-3 ጸሐፊው ተደራሲያኑን ያሳሰበበትን አድምጡ፡-

> ***... ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤ .... እርሱ ከሙሴ ይልቅ የሚበልጥ ክብር የተገባው ሆኖ ተቆጥሮአልና። (ዕብራውያን 3፡1-3)***

ኢየሱስ፣ ልክ እንደ ሙሴ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነ ጸሐፊው ይጠቅስና፣ ኢየሱስ ግን "የሚበልጥ ክብር የተገባው ሆኗል" ይላል፡፡

እነዚህን ጥቅሶች ተከትሎ፣ በ3፡7-19 ውስጥ፣ በሙሴ ላይ እንዳመፁት እንደ እስራኤላውያን ከልብ ድንዳኔና ከአመፅ እንዲርቁ ጸሐፊው ተደራሲያኑን ያስጠነቅቃል፡፡ ጸሐፊው ይህንን ማሳሰቢያውን የሚያጠናክረው ሙሴን ይከተሉ ከነበሩት አብዛኞቹ በእግዚአብሔር ላይ ከማመፃቸው የተነሳ ወደ ተስፋዩቱ ምድር እንዳልገቡ በማመልከት ነው፡፡ በተመሳሳይም መንገድ፣ የክርስቶስም ተከታዮች የክርስቶስን ክብር የሚካፈሉ የመጀመሪያ እምነታቸውን እስከፍፃሜ አፅንተው ሲጠብቁ ብቻ ነው፡፡ ያለማመን እስራኤላውያንን ከተስፋዩቱ ምድር አስቀርቷቸዋል፤ አለማመን በክርስቶስ ያሉትንም እንዲሁ ያደርጋቸዋል፡፡

በዕብራውያን 4፡1-13፣ ጸሐፊው ክርስቶስንና ሙሴን በመከተል መካከል የቀረበውን ንፅፅር ሰፋ አድርጎ ያቀርበዋል፡፡ ተደራሲያኑ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት ለመግባት የተቻላቸውን ሁሉ እንዲያደርጉ ያሳስባቸዋል፡፡ ብሉይ ኪዳንን በመጠቀም፣ ወደ እግዚአብሔር እረፍት መግባት ገና ወደፊትም እንደሚፈፀም ያብራራቸዋል፡፡ ሁሉ ነገር በእግዚአብሔር ቃል ፊት የተራቆተ መሆኑን

ያብራራላቸዋል፡፡ መልስን የሚሰጡት በእግዚአብሔር ፊት ነው፡፡ እናም በምድረ በዳ እንደቀሩት እንደ እስራኤላውያን ከመሆን ይልቅ ወደ እርሱ ዕረፍት ለመግባት ሊጋደሉ ይገባል፡፡

# የመልከጼዴቅ ክህነት 4፡14-7፡28

የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ መላእክት መገለጥና ስለ ሙሴ ሥልጣን ካወሳ በኋላ፣ በዕብራውያን 4፡14-7፡28 ውስጥ ስለ መልከጼዴቅ የንጉሥ ካህንነት በማንሳት የአይሁድ መምህራንን ይሞግታል፡፡

*ቀደም ባለው ትምህርታችን፣ በቁምራን ስለተገኘውና 11QMelchizedek* or *The Midrash on Melchizedek* ስለተባለው ምንባብ ጠቅሰናል፡፡ ምንባቡም መልከጼዴቅን እንደ ሰማያዊ አካልና በመጨረሻውም ዘመን የመጨረሻውን የመደምደሚያ ስርየት በፈፀም የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ እንደሚሆን ይገልፃል፡፡ ከቀደምት ተደራሲያኑ መካከል አንዳንዶቹ በዚህ ዐይነቱ ትምህርት ግልፅ ግራ መጋባት ውስጥ ገብተው ነበር፡፡ ነገሩም፣ መልከጼዴቅን መጠበቅ ትተው ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር የንጉሥ ሊቀካህን ለምን ይጠብቃሉ? እናም የዕብራውያን ጸሐፊ ኢየሱስ እንደ መልከጼዴቅ ሥርዓት እውነተኛ የንጉሥ ካህን መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህ አንጓ በአራት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ አንደኛውና ሦስተኛው ክፍሎች ክርስቶስን ከመልከጼዴቅም የሚልቅ አድርገው እንዲይዙት ያሳስባሉ፣ ሁለተኛውና አራተኛው ደግሞ ምክንያቱን ይነግሩናል፡፡

በዕብራውያን 4፡14-16፣ ጸሐፊው የመልከጼዴቅን ርዕሰ ጉዳይ የሚያነሳው ተደራሲያኑ እምነታቸውን አፅንተው እንዲይዙ ለማሳሰብ ነው፡፡ ኢየሱስ ፍፁም ሰው፣ ኃጢአት የሌለበት፣ ታላቅ ሊቀካህንና አማኞች በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ሊረዳቸው የሚችለውን ጸጋና ምህረት እንዲቀበሉ ለማድረግ ወደ ሰማይ የወጣ መሆኑን አፅንዖት በመስጠት ያበረታታቸዋል፡፡

በ5፡1-10፣ ኢየሱስ እንዴት እንደ መልከጼዴቅ ሥርዓት የንጉሥ ሊቀ ካህን ሊሆን እንደቻለ የዕብራውያን ጸሐፊ ያብራራል፡፡ ኢየሱስ በመታዘዙና በመከራው የክህነትን መመዘኛ አሟልቷል፡፡ ሆኖም ለዚህ ሥልጣን የይገባኛል ጥያቄ አላቀረበም፡፡ ጸሐፊው ከመዝሙር 2፡7 እና ከመዝሙር 110፡4 በመጥቀስ፣ እስራኤላውያን ከመልከጼዴቅ ይጠብቁት የነበረው ተስፋ በዳዊት ስርወ-መንግሥት እንደሚፈፀም ያመለክታል፡፡ እናም ኢየሱስ እንደ መልከጼዴቅ ሹመት የንጉሥ ሊቀካህን ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ወስኗል፡፡ በዚህ መንገድ፣ ለሚታዘዙት ሁሉ የዘላለም ድነት ምንጭ ሆኗል፡፡

ዕብራውያን 5፡11-6፡12 የዕብራውያን ተደራሲያን ከመጀመሪያ ትምህርት ወደ በሰለው ትምህርት እንዲሸጋገሩ ረዘም ያለ ማሳሰቢያ ያቀርብላቸዋል፡፡ ጸሐፊው ስለ ክርስቶስና ስለ መልከጼዴቅ ያቀረበውን ትምህርት ተደራሲያኒ ሊረዱ እንደሚያዳታቸው ይገነዘባል፡፡ ሆኖም በመረዳት ባለጠግነት እንዲያድጉና ከክህደት እንዲጠበቁ ያበረታታቸዋል፡፡ በአንዱ እውነተኛ የንጉሥ ታላቅ ሊቀካህን ካለመኑ፣ ዳግመኛ የኃጢአት ስርየት እንደማይቀርላቸው ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ ጸሐፊው ለተደራሲያኑ ትልቅ ተስፋ አለው፣ ሆኖም ከስንፍናቸው ሊመለሱና እግዚአብሔር የገባላቸውን የተስፋ ቃል ለመውረስ በእምነት የፀኑትን እንዲመስሉ ያሳስባል፡፡

በዕብራውያን 6፡13-7፡28፣ ጸሐፊው ኢየሱስ የመልከጼዴቅ የንጉሥ ሊቀካህንነት ፍጻሜ ስለመሆኑ የጀመረውን ዘገባ ይቀጥልበታል፡፡ በተለይም፣ የኢየሱስ የንጉሥ ካህንነት፣ ከሌዋውያንኑ ክህነት እጅግ የሚልቅ መሆኑን ያብራራል፡፡ ዕብራውያን ሲጻፍ በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ይደረግ የነበረው ሥርዓት እንደቀጠለ ነበር፡፡ ይህም እውነታ የኢሱስ ሞት በመቅደስ ውስጥ የሚደረገው የሌዋውያን የመስዋዕት ሥርዓት ማክተሚያ ነው የሚለውን የክርስትና አዋጅ የሚፈታተን ነበር፡፡ ለዚህ ተግዳሮት ምለሽ ለመስጠት፣ ጸሐፊው የአይሁድ መምህራን መልከጼዴቅ በመጨረሻው ዘመን መስዋዕትን ያስቀራል ብለው የሚያስተምሩትን በማንሳት ይጠቅሳል፡፡ የሚደመድመውም ኢየሱስ የዳዊት ታላቅ ልጅ፣ እንደ መልከጼዴቅ ሹመት ዘላለማዊ የንጉሥ ካህን ነው ብሎ እግዚአብሔር የማለበትን መዝሙር 110፡4 በመጥቀስ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ኢየሱስ የሌዋውያኑ የመስዋዕት ሥርዓት ማክተሚያ ሆኗል፡፡

ኢየሱስ ከሌዋውያን ክህነት የሚልቅ መሆኑን ለማሳየት፣ ጸሐፊው በዘፍጥረት 14፡20 መልከጼዴቅ ከእርሱ የሚልቅ መሆኑን ለማሳየት አብርሃም ዐሥራት እንደከፈለ ይጠቅሳል፡፡ ስለዚህም፣ የአብርሃም ዘር የሆነው ሌዊ፣ በአርሃም አማካይነት ተምሳሊታዊ በሆነ መንገድ ያንኑ አደርጓል ማለት ነው፡፡ እናም፣ ክርስቶስ እንደ መልከጼዴቅ ሹመት የንጉሥ ሊቀካህን እንደመሆኑ መጠን፣ ከሌዋውያን ክህነት እጅግ ሊልቅ ይገባዋል፡፡ የሌዋውያን መስዋዕት ፍፁም ስርየትን አያስገኝም፣ ክርስቶስ ግን የመልከጼዴቅ የንጉሥ ክህነት ፍፃሜ እንደመሆኑ ለአንዴና ለመጨረሻ ስርየትን አድርጓል፡፡

**ለሰባኪያችና ለአስተማሪዎች፣ ከዕብራውያን መጽሐፍ ተወዳጅ ክፍሎች መካከል አንዱ፣ በብሉይ ኪዳን ማንነቱ በውል አይታወቅም በሚባለው ካህን እና ኢየሱስ መካከል የቀረበው ንፅፅር ነው፡፡ ጸሐፊው ይህንን ማነፃፀሪያ ከማቅረቡ በፊት፣ በሌዋውያኑ የአሮን ክህነት መካከል ንፅፅር ያደርጋል፡፡ የአሮን ክህነት ከዘር የሚወረስ ነው፤ ከአባት ወደ ልጅ ይተላለፋል፣ ነገዱም የሌዊ ነገድ ነው፡፡ የኢየሱስ ክህነት ግን እንዲህ አይደለም፡፡ እርሱ ከሌዊ ወገን ሳይሆን ከይሁዳ ነገድ ከዳዊት ወገን ነው፡፡ ምክንያቱም የአሮን ክህነት ይጠፋል፣ የአሮን ክህነት ከአባት ወደ ልጅ ይተላለፋል፡፡ በዚህ ተቃራኒ ግን፣ የኢየሱስ ክህነት ለዘላለም ነው፡፡ የእርሱ ክህነት ከዘላለም እስከ ዘላለም ነው፤ እርሱ ዛሬም ያው ካህን ነው፡፡ መልከጼዴቅ ካህን የመሆን ሰብዓዊ መብት የለውም፣ ሆኖም በታሪክ ውስጥ በእግዚአብሔር የተመረጠ ካህን ሆኖ ተገልጦ ተሰውሯል፡፡ ኢየሱስም ያንኑ በማድረግ በምድር አገልሎቱ ማብቂያ ከትንሣኤው በኋላ ወደ ሰማይ አርጓል፡፡ ዶ/ር አልቪን ፓዲላ**

**በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ሁለት ዓይነት ክህነቶች ተጠቅሰዋል፡፡ አንደኛው ትውፊታዊውና በአሮን ተጀምሮ በሌዊ ነገድ እየተከናወነ የዘለቀው፣ የሌዋውያን ክህነት ነው፡፡ ከዚያም ባልተለመደ መንገድ ቀደም ባለው የአባቶች ዘመን፣ በአብርሃም ዘመን ብቅ ያለው የመልከጼዴቅ የጌታ ካህን፣ የጌታ ሊቀ ካህን፣ ክህነት ነው፡፡ እናም ኢየሱስ ከሁለቱም ጋር ተነፃፅሯል፣ በአንድ በኩል ከሌዋውያን ክህነት የሚልቅ መሆኑን ለማሳየት፣ በሌላ ጎን ደግሞ በሊቀ ካህንነቱ ከመልከጼዴቅ ጋር ለየት ባለ መንገድ የሚስተያይበት ሲሆን፣ የእርሱ ክህነት ግን የዘላለም ነው፡፡ ስለ መልከጼዴቅ የምናውቀው ወላጆች የሌሉት መሆኑን፤ ወደ ገሃዱ ዓለም የመጣበት ምንም ዝርያ እንደሌለው፤ ከአብርሃም እጅግ የሚልቅ ነበር ምክንያቱም አብርሃም ለእርሱ ዐሥራት አውጥቷል፣ ዐሥራት የሚከፍለውም ታናሹ ለታላቁ መሆኑ**

***ይታወቃል፡፡ ግን ያ የሊቀ ካህን ሥርዓት፣ በሁሉ ረደግ ከሁሉ የሚበልጠው ከህዝብ ሁሉ ማለትም በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ይሁዲነትን ከመሠረቱት አባቶች ሁሉ ዐሥራትን ይቀበላል፣ ያም የመልከጼዴቅ አምሳያ የሚጸና ነው፡፡ የክርስቶስ ክህነት፣ አዲሱ ክህነት የሚከናወነው እንደ መልከጼዴቅ ሥርዓት ነው፡፡ ዶ/ር ኤድዋርድ ኤም፣ ኬዘሪያን***

# አዲሱ ኪዳን 8፡1-11፡40

አራተኛው ዐቢይ አንጓ፣ በዕብራውያን 8፡1-11፡40 የሚገኘው፣ በአዲሱ ኪዳን ላይ ያተኩራል፡፡ በዚህ ስፍራ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ አዲሱ ኪዳን የአሮጌው የበላይ እንዴት እንደሆነ በማውሳት ክርስቶስ በእግዚአብሔር የተቀባው የንጉሥ ሊቀ ካህን ስለመሆኑ ያብራራል፡፡

"አዲስ ኪዳን" የሚለው ቃል የተወሰደው ከኤርምያስ 31፡31 ነው፡፡ በዚህ ጥቅስ፣ ነቢዩ የሚተነብየው በመጨረሻው ዘመን እስራኤልና ይሁዳ ከተጋዙ በኋላ እግዚአብሔር ስለሚሰጣቸው የፍፃሜ ተሃድሶ ኪዳን ነው፡፡ ይኸው ተመሳሳይ የነገረ ፍፃሜ ኪዳን በኢሳያስ 54፡10 እና በሕዝቅኤል 34 እና 37 የሰላም ኪዳን ተብሎ ተጠርቷል፡፡ እናም፣ በዚህ ነጥብ፣ የዕብራውያን ጸሐፊ በመጨረሻው ዘመን ስለሚመጣው ስለ መልከጼዴቅ የጀመረውን ሃሳብ ይገታና ወደ አዲሱ ኪዳን ዘወር ይላል፡፡

ይህ የዕብራውያን አንጓ ስምንት ዐቢይ ክፍሎችን ይዟል፡፡ በመጀመሪያ፣ ዕብራውያን 8፡1-13 ኢየሱስ በሰማያት ያለፈ የአዲሱ ኪዳን መካከለኛ የመሆኑን ሃሳብ ያስተዋውቃል፡፡

በቁጥር 1 እና 2፣ ጸሐፊው "የተናገርነውም" በማለት ነጥሎ ይገልጣል፡፡ ክርስቶስ፣ ታላቁ የንጉሥ ካህን፣ "በሰው ሳይሆን፣ በጌታ በተሠራችው እውነተኛ ድንኳን" በሰማያት እያገለለ መሆኑን ያብራራል፡፡

በሌላ አባባል፣ የሌዋውያን ክህነት በምድር ያንን ተግባር አከናውኗል፡፡ ክህነታቸው የተመሠረተው ግን በህግ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ ከሙሴ ጋር የተፈፀመው ኪዳን ምድራዊውን የሌዋውያን ክህነት መሥርቷል፣ ከእስራኤል ኃጢአት የተነሳ ግን አልተሳካም፡፡

በንፅፅሩ፣ በኤርምያስ 31 የተቀመጠው ኪዳን አይወድቅም፣ ዕብራውያን 8፡6 እንዲህ ያስቀምጠዋል፡

***አሁን ግን በሚሻል ተስፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ... (ዕብራውያን 8፡6)***

እነዚህ "የሚሻሉ ተስፋዎች" የእግዚአብሔርን ህዝብ ፍፁም ተሃድሶ እና የኃጢአታቸውንም የዘላለም ይቅርታ ያስገኛሉ፡፡

በዕብራውያን 9፡1-28፣ የዕብራውያን ጸሐፊ የኢየሱስ ንጉሣዊ ክህነት ከሌዋውያን ክህነት ይልቃል የሚለውን ሃሳብ አስፋፍቶ ይገልፃል፡፡ ይህንን ክፍል የሚጀምረው ስለ ሙሴ ምድራዊ ድንኳን ሥርዓት በማውሳት ሲሆን፣ በዚያም ከእግዚአብሔር ሰማያዊ መቅደስ ጋር የሚመሳሰሉ ገፅታዎችን ይገልጣል፡፡ በተጨማሪም፣ በዘሌዋውያን 16፡34 ስለታዘዘው በዓመታዊው የስርየት ቀን ስለሚፈፀመው የክህነት ሥራ ያብራራል፡፡ ይህም የሚያሳየው በምድራዊው ድንኳን የሚቀርቡ

መስዋዕቶች የኃጢአትን ችግር ሙሉ በሙሉ ሊያስወግዱ የማይችሉ ሆኖም በየዓመቱ በተደጋጋሚ የሚደረጉ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ መስዋዕቶች ታሪክ በመጨረሻው ዘመን ጫፍ ላይ እስከሚደርስበት ወቅት ድረስ ይዘልቃል፡፡ ይህንንም በዕብራውያን 9፡10 "የአሁኑ ዘመን ምሳሌ" ይለዋል፡፡ በዕብራውያን 9፡11 እንዲህ በማለት ይጨምራል፡፡

*ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ፥ (ዕብራውያን 9፡11)*

ይህ ዐረፍተ ነገር በክርስቶስ ያመኑት እነርሱ ፍፁም በሆነው ስርየት ከኃጢአታቸው ስለመንፃታቸው እና በሰማያትም ወዳለው የጸጋ ዙፋን ለመግባት በሩ እንደተከፈተላቸው ያወሳል፡፡

***የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ኢየሱስ ስለ ኃጢአት ባቀረበው መስዋዕትና በብሉይ ኪዳኑ የመስዋዕት ሥርዓት መካከል ካቀረባቸው ንፅፅሮች አንዱ በብሉይ ኪዳኑ የመስዋዕት ሥርዓት የክህነቱ ሥራ በሙላት ሊከናወን የማይችል መሆኑ ነው፡፡ ካህኑ ደግሞ ደጋግሞ ስለ ኃጢአት መስዋዕት ያቀርባል፡፡ በዚህ ስፍራ ጸሐፊው ማስጨበጥ የፈለገው ነጥብ፣ ኃጢአትን ለማስወገድ ሊከናወን የተገባው ተግባር በሙላት ሊፈፀም አልተቻለም፣ የኢየሱስ ሥራ ግን ሙሉ በሙሉ ፈፅሞታል የሚለውን ነው፡፡ ኢየሱስ፣ ራሱን አንድ ጊዜ ለኃጢአት መስዋዕት አድርጎ ካቀረበ በኋላ፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል፣ ካህናቱ ግን ገና ሥራው ስለሚቀጥል በእግሮቻቸው ቆመዋል፡፡ ኢየሱስ ግን ተቀምጧል፣ የዕብራውያን ጸሐፊ ይህንን ሲፈታው፣ የተቀመጠው ሥራው ስለተጠናቀቀ ነው፣ የኃጢአትም ጉዳይ አብቅቶለታል፣ ተፈፅሟል፡፡ ዶ/ር ኮንስታንቲን ካምፐቤል***

ጸሐፊው በተጨማሪም የኢየሱስ መስዋዕት ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ያብራራል፡፡ የኑዛዜን ምሳሌ ይጠቀማል፡፡ ልማዳዊው ኑዛዜ የሚፀናው በአንድ ሰው ሞት ነው፡፡ የሙሴም ኪዳን በሞትና በደም የጸና ነው፡፡ እናም፣ አዲሱ ኪዳንም በሞትና በደም ሊፀና ይገባዋል በማለት ፀሐፊው ምክንያቱን ያቀርባል፡፡ በሰማያዊ ስፍራ በእግዚአብሔር ውስጠኛ መቅደስ በፈሰሰ የክርስቶስ ደም ማለት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ግን፣ "የኑዛዜው" ውርስ ይቅርታ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ሰዎች በክርስቶስ ደም እስኪነፁ ድረስ ይቅርታ ሊገኝ አይችልም ማለት ነው፡፡ በዕብራውያን 9፡26 ውስጥ ጸሐፊው እንዲህ ያስቀምጠዋል፡

*እንዲህ ቢሆንስ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል። (ዕብራውያን 9፡26)*

ደሙ የተረጨው በሰው ሠራሽ መቅደስ ውስጥ ስላልሆነ ኢየሱስ ኃጢአትን ለአንዴና ለዘላለም አስወግዷል፡፡ ራሱንም መስዋዕት በማድረግ ወደ ሰማያት ገብቷል፡፡ ይህም እግዚአብሔር በኤርምያስ 31፡34 እንደሰጠው ተስፋ ነው፡

*በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና። (ኤርምያስ 31፡34)*

ህዝቡን ከፍርድ ያድን ዘንድ ኢየሱስ መስዋዕት በመሆን ሞተ፡፡ ጸሐፊው ይህንን ክፍል የሚያጠናቅቀው ክርስቶስ እንደሚመለስ በመግለፅ ሲሆን፣ ሆኖም ስለ ኃጢአት መስዋዕት ሊያቀርብ ግን አይደለም፡፡ ኢየሱስ ሲመለስ፣ ለሚጠባበቁት የመዳናቸውን ሙላት ያመጣላቸዋል፡፡

ዕብራውያን 10፡1-18 የሙሴን ኪዳን ከዘዲሱ ኪዳን ጋር ማነፃፀሩን ይቀጥላል፡፡ በዚህ ወቅት፣ ጸሐፊው በአዲሱ ኪዳን፣ የኢየሱስ ሊቀካህንነት የመጨረሻውን የኃጢአት ይቅርታ አስገኝቷል፡፡ በማስተሰረያው ቀን ይቀርቡ የነበሩ መስዋእቶች በየዓመቱ የሚቀርቡ የኃጢአት ማሳሰቢያዎች እንጂ ኃጢአትን ሊያስወግዱ የሚችሉ አለመሆናቸውን በድጋሚ ያነሳል፡፡ የእንስሳት መስዋእቶች እግዚአብሔርደስ እንደማያሰኙ እውቅና ይሰጣል፡፡ ዳዊት ራሱን እንደ እውነተኛ አርዓያ ለእግዚአብሔር ማቅረቡን ከመዝሙር 40 ይጠቅሳል፡፡ ኢየሱስም ራሱን በመስቀል ላይ መስዋዕት አድርጎ በማቅረብ ይህንን አርዓያነት መፈፀሙን ያብራራል፡፡ የሌዋውያኑ መስዋዕቶች ፍፁም የሆነውን የኃጢአት ይቅርታ እስካላስገኙ ድረስ፣ ኤርሚያስ የተነበየው አዲሱ ኪዳን እግዚአብሔር የህዝቡን ኃጢአት ለዘላለም ይቅር የሚልበትን ተስፋ ይሰጣል፡፡ ኢየሱስም ያንን ፈፅሞታል፡፡ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲያ የእንስሳት መስዋዕት ፈፅሞ አያስፈልግም፡፡

ዕብራውያን 10፡19-23 በአራት የተከፈለው ማሳሰቢያ የመጀመሪያው ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ተደራሲያኑ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡና ተስፋቸውን አፅንተው እንዲይዙ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ ክርስቶስ፣ በገዛ ደሙ፣ የቅድስተ ቅዱሳኑን በር እንደከፈተው ያብራራል፡፡ እናም ቁጥር 23 እንደሚነግረን፣ "እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ" ምክንያቱም እግዚአብሔር የታመነ ነውና፡፡

በ10፡24-31፣ ተደራሲያኑ "ለፍቅርና ለመልካም ሥራ" እርስ በርስ እንዲበረታቱ ጸሐፊው ያሳስባል፡፡ የፍርድ ቀን እየቀረበ ሲመጣ፣ ዘወትር መሰብሰባቸውን እየጨመሩ እንዲሄዱ ይነግራቸዋል፡፡ ከዚያም በመቀጠል "የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ፣ የኪዳኑንም ደም እንደ እርኩስ ነገር የቆጠረና የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ" ስለሚጠብቀው የሚበልጥ ፍርድ ያብራራል፡፡ እንደጠቀሰውም፣ እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ ይፈርዳል፡፡

በዕብራውያን 10፡32-35፣ ተደራሲያኑ የቀደመውን ዘመን እንዲያስቡና ድፍረታቸውን እንዳይጥሉ ጸሐፊው ጥሪ ያቀርብላቸዋል፡፡ በሚመጣው ዘመን የተሻለና ዘላለማዊ ብድራት እንዳላቸው በማወቅ ባለፉት ዘመናት በፍፁም ፈቃድና በደስታ መከራን እንደተቀበሉ ያስታውሳቸዋል፡፡ በዚህ መንገድ ከቀጠሉ፣ ታላቅ ብድራት ይጠብቃቸዋል፡፡

በዕብራውያን 10፡36-39 ተደራሲያኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈፀም እንዲፀኑ ያሳስባቸዋል፡፡ ማሳሰቢያውንም የሚያጠናክረው እግዚአብሔር በፍፃሜው ፍርድንና በረከትን እንደሚያመጣ በማስታወስ ነው፡፡ እግዚአብሔር በእምነታቸው በሚያፈገፍጉት ደስ እንደማይሰኝ ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ በዕብራውያን 10፡39 በተጨማሪ እንዲህ ይላል፡

> ***እኛ ግን ነፍሳችውን ሊያድኑ ከሚያምኑቱ ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉ አይደለንም። (ዕብራውያን 10፡39)***

**መልካም፣ እነሆ አይሁድ አማኒያን ደክመዋል፣ ዝለዋል፣ በመከራም ውስጥ ናቸው፡፡ ጉዳዩ በቤተክርስቲያን የታሪክ ዘመን ሁሉ ክርስቲያች ይኸው ይደርስባቸዋል፡፡ እነዚህ ግን ደክመዋል እናም እምነታቸው እዋዠቀ ነው፡፡ እናም፣ ቤታቸው ምስቅልቅሉ ወጥቷል፡፡ እስከመስዋዕትነት የሚያደርስ ፈተና ገና አልገጠማቸውም ሆኖም፣ ከአድማስ ባሻገር እየገሰገሰ የሚመጣ ይመስላል፣ ስለዚህ በእምነታቸው ገና በርካታ ፈተና ይጠብቃቸዋል፡፡ እናም ሁሉን እርግፍ አድርገው ወደ አሮጌው መንገዳቸው እንዲመለሱ የሚገፈትራቸው ብዙ ነው፡፡ ስለዚህ የዕብራውያን ጸሐፊ በክርስቶስ ወደማመን ለመጡበት ለአዲሱ ኪዳን እውነተኛ ሆነው ይዘልቁ ዘንድ ሊያበረታታቸው ይጽፍላቸዋል፡፡ ዶ/ር ኬ. ኤሪክ ቶኔስ**

ይህንን ተከታታይ ማሳሰቢያ በማስከተልም፣ ጸሐፊው በ11፡1-40 ውስጥ ትኩረቱን ወደሚያድነው እምነት ዘወር ያደርጋል፡፡ የዕብራውያን ተደራሲያን ቀደም ባሉ ዘመናት በመከራ ያለፉ ከዚያም የበለጠን መከራ ለመቀበልም ዝግጁ እንደነበሩ ቀደም ብለን ጠቅሰናል፡፡ ስለዚህ በመከራ ወቅት እንዳያፈገፍጉ ጸሐፊው ያበረታታቸዋል፡፡

ከዚያም በማስከተል በመከራ ውስጥ ጸንተው ያለፉ በርካታ የብሉይ ኪዳን የእምነት አባቶችን በመዘርዘር ሊል የፈለገውን ያመለክታቸዋል፡፡ እነዚህ የታመኑ አባቶች በሕይወት ዘመናቸው፣ የተገባላቸውን የተስፋ ቃል አልወረሱም ምክንያቱም የእግዚአብሔር ተስፋ ለሩቅ ዘመን ነበርና ነው፡፡ ሆኖም፣ የዕብራውያን ጸሐፊ እንዳብራራው፣ ክርስቶስ ተመልሶ ሲመጣ ጸሀፊውና ተደራሲያኑ በክርስቶስ ፍፁማን ይሆናሉ፡፡

## ተግባራዊ ፅናት 12፡1-13፡25

የመጨረሻው ዐቢይ አንጓ፣ በዕብራውያን 12፡1-13፡25 በተግባር የመፅናትን መሪ ሃሳብ በማብራራት የዕብራውያንን መጽሐፍ ወደ ድምዳሜው ያመጣዋል፡፡ ይህ አንጓ ረጃጅም ማሳሰቢያዎችንና ማብራሪያቸውን ይዟል፡፡ ለእኛ ዓላማ ን፣ ማሳሰቢያዎቹን ጠቅለል አድርገን እናቀርባለን፡፡

የዕብራውያን ጸሐፊ ወደ መጽሐፉ መደምደሚያ ሲገሰግስ፣ ስለ ሕይወት የተለያዩ ጉዳዮች ፈጠን ፈጠን እያለ ማሳሰቢያ ይሰጣል፡፡ በብዙ ረገድ፣ ይህኛው ክፍል በተግባራዊ ነገሮች ላይ ያተኮረ ነው፣ በተለይም፣ ተደራሲያኑ እንዲከታተሏቸው በሚፈልጋቸው ባህርያት ላይ ያተኩራል፡፡ ጸሐፊው ከዚህም ባሻገር ይህንን እድል በመጠቀም የክርስቶስ ተከታዮች የሚያገኟቸውን ታላላቅ በረከቶች አርቀው እንዲያዩ ያበረታታቸዋል ልባቸውንም ያሞቀዋል፡፡

እነዚህ ማሳሰቢያዎች መደምደሚያውን በማስከተል በአምስት ጥቅል ጎራዎች ይከፈላሉ፡፡ በዕብራውያን 12፡1-3፣ ልክ እንደ ሯጭ፣ ተደራሲያኑ እንዲፀኑ ያሳስባል፡፡ ይህንንም ለማድረግ ኃጢአትን በማስወገድ፣ እስከ ፍፃሜ የፀናውን ክርስቶስን መመልከት ይገባቸዋል፡፡

ዕብራውያን 12፡4-13፣ መከራን ከእግዚአብሔር እንደተቀበሉት የአባት ቅጣት በመቁጠር እንዲፀኑ ያሳስባል፡፡ ጸሐፊው ይህንን አስተሳሰብ የሚደግፈው ከምሳሌ 3፡11-12 በመጥቀስ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ቅጣት “የጽድቅንና የሰላምን ፍሬ ያፈራል” በማለት ያብራራል፡፡ ስለዚህ በመከራ ሊበረቱ እንጂ ሊሸመደመዱ እንደማይገባ ያበረታታቸዋል፡፡

በዕብራውያን 12፤14-17፣ ተደራሲያኑ እርስ በርስ እንዲበረታቱ እንደገና ያሳስባቸዋል፡፡ በሰላምና በቅድስና እንዲነሩ ይመክራቸዋል፡፡ በዝሙት እርኩሰት ማንም ወድቆ እንዳይገኝ ያስጠነቅቃል፡፡ ብኩርናውን ያቃለለው ኤሳው መልሶ ሊያገኘው እንዳልቻለ በመጥቀስ የጉዳዩን ጥብቅነት ያመለክታቸዋል፡፡

በዕብራውያን 12፡18-29፣ በክርስቶስ ስላገኙት በረከት አመስጋኞች እንዲሆኑ ጸሐፊው ተደራሲያኑን ያሳስባል፡፡ የተደራሲያኑን መንፈስ ለማነቃቃትና እንዲፀኑ ለማበረታታት፣ ሊቆጠሩ የማይችሉ በረከቶቻቸውንና ዕድሎቻቸውን ያስታውሳቸዋል፡፡ ዕብራውያን 12፡22-24 የተጻፈውን አድምጡ፡

> ***ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል። (ዕብራውያን 12፡22-24)***

በእብራውያን 12፡22 እና ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች፣ የዕብራውያን ጸሐፊ “ወደ ጽዮን ደርሰናል” ይላል፡፡ እንግዲህ ጉዳዩን ከቀደመው ምእራፍ ጋር ማስተያየት ይገባል፡፡ የእምነት ምዕራፍ ብለን በምንጠራው ምዕራፍ 11 ውስጥ፣ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ተስፋቸውን ሳይቀበሉ በእመነታቸው ጸንተው ዐለፉ ተብሎ ተነግሮናል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ግን፣ በምእራፍ 12 መግቢያ ላይ፣ ክርስቶስ መምጣቱ ይነገረናል፣ ክርስቶስም ሩጫውን ፈፀመው፤ ሁሉንም ድል ነሣ፡፡ እናም፣ ቁጥር 22 እና ቀጥለው ያሉት ቁጥሮች የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በምድር ዘመናቸው ወዳልገቡበት ስፍራ ገብተናል ነው የሚሉት፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ በመቀጠልም፣ *“ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደተጻፉ ወደ በኵራት ማኅበር መጥተናል” ይላል፡፡ እየገለፀ ያለው በዚያ በሰማያዊ ስፍራ የእግዚአብሔር ህልውናና የእግዚአብሔር ዙፋን አለ ነው፡፡ ከዚህ መግለጫ ግራ አጋቢ ከሚመስሉ አንድምታዎች አንዱ በብሉይ ኪዳን የተመለከቱት የጽዮን ተራራ እና ኢየሩሳሌም አሁን በክርስቶስ ላመኑ እውን ሆነው ተሰጥተዋል የሚለው ነው፡፡ ስለዚህ መዝሙር 48 የመሳሰሉ ማለትም፣* እግዚአብሔር ትልቅ ነው በአምላካችን ከተማ በተቀደሰ ተራራ ምስጋናው ብዙ ነው። *የሚለውን በትክክል መመልከት እንችላለን፡፡ እኛ በምድር እንደ ክርስቶስ ጉባኤ በአንድነት ስንሰበሰብ ምን ትርጉም ይሰጠናል? ብለን ማሰብ ይገባናል፡፡ እኛ የቆምነው በምድር ባለችው በተምሳሊቷ ሳይሆን በሰማያዊቷ በእውነተኛዋ ጽዮን ነው፣ እርሷም በአዲስ ሰማይና ምድር የምትገለጠውና ከሰማይ የምትወርደው ኢየሩሳሌም ናት፡፡ በዚያም እኛ ሁሉን ድል ባደረገው በክርስቶስ አማካይነት በእግዚአብሔር ፊት እንቆማለን፡፡*

*ይህም ነገር በምትታየዋ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚኖረንን ዕይታ የሚያቀና አተያይ ነው፡፡*
*ቄስ ሚካኤል ጄ.ግሎዶ*

በዕብራውያን 13፡1-19፣ ተደራሲያኑ በዕለት ከዕለት ሕይወታቸው ታማኝ እንዲሆኑ ጸሐፊው ያበረታታቸዋል፡፡ እርስ በርስ መዋደድን፣ በውጪ ያሉትንና እስረኞችን ማሰብን፣ ትዳርን ማክበርን፣ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን፣ መሪዎቻቸውን ማሰብን ይጠቅስላቸዋል፡፡ በተጨማሪም የክርስቶስን መከራ በሕይወታቸው ለመካፈል ሲሉ በዙሪያቸው ያለውን የአይድን እንግዳ ትምህርት እንዲቃወሙ ያሳስባቸዋል፡፡ የምሥጋና መስዋዕትን እንዲያቀርቡ፣ መልካምን እንዲያደርጉና እርስ በርስ እንዲረዳዱ ያሳስባቸዋል፡፡ ለው ለእርሱና ለባልደረቦቹ እንዲጸልዩለት በመለመን ይህንን ክፍል ይደመድማል፡፡

በመጨረሻም፣ በዕብራውያን 13፡20-25፣ ጸሐፊው መጽሐፉን ይደመድማል፡፡ በቁጥር 20 እና 21፣ ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው፣ እግዚአብሔር፣ በእነርሱ ውስጥ እንዲሠራና ክብርንና ምሥጋናን እንዲቀበል በመጸለይ የመሰናበቻ ቡራኬ ያቀርባል፡፡ ከዚያም በቁጥር 22፣ ለተደራሲያኑ "የምክርን ቃል እንዲታገሡ" ወይም ለእነርሱ ያቀረበውን መልእክት እንዲቀበሉ ጥሪ ያቀርባል፡፡ ደብዳቤውንም በተለያዩ ሰላምታዎች ይደመድማል፡፡

# ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት፣ የዕብራውያንን መጽሐፍ አወቃቀርና ይዘት ተመልክተናል፡፡ በክርስቶስ በሚመጣው የመጨረሻው ዘመን ተከታታይ ይዘት ላይ አትኩረናል፣ የጸሐፊውን አመለካከት የሚደግፉ የብሉይ ኪዳን ክፍሎችን አይተናል፣ ስለ መጽናት ያቀረባቸውንም ማሳሰቢያዎች ዳስሰናል፡፡ የክርስትናን እምነት አስመልክቶ በአካባቢያቸው ካሉ የአይሁድ አስተምህሮዎች የሚገጥማቸውን ፈተና ሊወጡ የሚችሉበትን መንገድ ለማሳየት ያቀረባቸውን ተከታታይ መሪ ሃሳቦች እንዴት እንዳስተሳሰራቸው በማመልከት የመጽሐፉን አሳማኝ አወቃቀር ተመልክተናል፡፡

የዕብራውያን መጽሐፍ ለክርስቶስ ተከታዮች ታላቅ ቅርስ ነው፡፡ ነገረ-መለኮታዊ ትንታኔው ክርስቶስ ለእኛ የሠራቸውን ሥራዎች ሁሉ በጥልቀት ይዳስሳል፡፡ ክርስቶስን መከተል ማለት ምን ማለት እንደሆነም ልብን ዘልቆ የሚገባ መልእክት አለው፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሥልጣኖቻችን ሁሉ ምንጭ ወደ ማድረግ እንድንመለስ እና ክርስቶስንም የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሁሉ ፍፃሜ አድርገን እንድንቀበል ጥሪ ያቀርብልናል፡፡ እርሱ ለእኛ ያዘጋጀልንን፣ ያቺን የማትናወጠዋን መንግሥት እስከምንወርስባት እስከዚያች ቀን ድረስ በምሥጋና በተሞላ ልብ ክርስቶስን እንድንወድድና እንድናገለግል ይማፀነናል፡፡